

በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የክርስትና እምነት የተመሠረተባት ጥንታዊት አክሱም ጽዮን

# ትንሣኤ



እስራኤላውያን በቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት ኤርትራን ሲሻገሩ ግብጻውያን እንደሰጠሙ።
«የእግዚአብሔር መልአክ ቅ ሚካኤል በእስራኤል ሠራዊት ፊት ይሄድ ነበር» (ዘጸአ.14.19)

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር 26 ሕዳር ፲፱፻፸፱ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረ ጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይ ሟል ።


አዘጋጅ

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐዋርያዊ ድርጅት

የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ

በወር አንድ ጊዜ

እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616

የመልእክት ሣ.ቁ. 3137

አዲስ አበባ


ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ለምን አንድ አይሆኑም? | ፪ |
| ዓሣ ከባሕር ከወጣ ነፍሱን አጣ | ፫ |
| ምን እንርዳዎ | ፬ |
| የኢትዮጵያውያን ቀደምትነት በተቀደሱ ቦታዎች | ፭ |
| የሃይማኖት ዐምድ | ፮ |
| አስተያየት ከአንባቢዎቻችን | ፯ |
| ይህን ያውቁ ኖሯል? | ፰ |
| የጤና ዐምድ | ፱ |
| ዜና ሀገረ ስብከት | ፲ |
| ዜና አብያተ ክርስቲያናት | ፲፩ |
| ሊቃውንቶቻችን | ፲፪ |
| ክርስቲያናዊ ሕይወት | ፲፫ |
| ልማት በቤተክርስቲያን | ፲፬ |
| የወጣቶች ዐምድ | ፲፭ |
| ጥረታችን ለማትረፍ እንጂ ለማጉደል አይደለም | ፲፮ |
| ሐዋርያት ለተረሱ ሕዝቦች | ፲፯ |
| ሥነ ጽሑፍ በኢትዮጵያ | ፲፰ |
| የመጽሐፍ ቅዱስ ዐምድ | ፳ |
| ፊደል | ፳፩ |


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በቤተ ክህነት ውስጥ የሚሠራበትን ማኅተም ተመልክታችሁ እንደሆነ "ኦርቶዶክስ" ብቻ ይላል እንጂ "ተዋሕዶ" አይልም ለምን ? ከሌላ ኦርቶዶክስ በምን እንለያለን?

ዲ/ን.ገ.ሕ.ኪ

● አዎ እርሶ እንዳሉ እኛም ማኅተሙን ባየን ጊዜ ተዋህዶ የሚለው ቃል አልተጨመረበትም፣ ይህ ቃል በእርግጥ ከሌሎች የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስትያናት የምንለይበት ስለሆነ ቢጨመር መልካም ነው ፤የቤተ ክህነት ብቻ ሳይሆን የልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ድርጅቶችም በማኅተማቸው ላይ ተዋሕዶ የሚለው ቃል አልቀረበም ስለዚህ በተዋሕዶ እምነታችን ስለማናፍርበት በማኅተማችን ተዋሕዶ የሚለው ቃል ይኑር እንላለን።

★★★

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከሁሉ አስቀድሜ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም እላችኋለሁ። በቁጥር 22 ትንሣኤ መጽሔት "ዝናም ለዘር" በሚለው ርእስ አንቀጽ ላይ "ኢሀዴጋ ለምድር እምቅድመ ዓለም ወእስከ ለዓለም እግዚአብሔር ምድርን ከዓለም በፊት ጀምሮ እስከ ዘላለም ያለ ካህናትና ዲያቆናት አልተዋትም በማለት ሊቁ ቅዱስ ያሬድ የተናገረው ቃል ምንም እንኳን መንፈሳዊ ትርጓሜ ቢኖረውም ይልና ሌላ ወቅታዊ ትርጉም ይሰጠዋል። ይሁን እንጂ "እምቅድመ ዓለም ወእስከ ለዓለም" ሲል ቀሳውስትና ዲያቆናት ዓለም ሳይፈጠር ነበሩ ማለት ነው? ስላልገባኝ እንዲያብራሩልኝ እጠይቃለሁ ።

ዲያቆን የሸዋሰው ነጋሽ
ከጋሙ ጎፋ ክ/ሀገር

● ዲያቆን የሸዋሰው የመጽሔታችን ተከታታይ በመሆንህ እጅግ እናመሰግንሀለን የቅ/ያሬድ ቃል ቀሳውስትና ዲያቆናት ከዓለም በፊት ነበሩ ማለትን አያመለክትም ። ግን ከጥንት ጀምሮ ማለት እንደሆነ ይተረጐማል ምክንያቱም ከዓለም በፊት ምድር ነበረች አይባልምና ።

★★★

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በጐጃም ክፍለ ሀገር በብቸና አውራጃ በነማይ ወረዳ 82 አብያተ ክርስትያናት አሉ ከነዚህም አብያተ ክርስትያናት አብዛኞዎቹ ያሉአቸው ምዕመናን በጣም ጥቂቶች ስለሆኑ በሰበካ ጉባኤ በሚወጣው ገንዘብ የጥንቱንና ዘመናዊውን ትምህርት አጣምሮ የሚያስተምር ት ቤት ለማቋቋም አስበን አልተሳካልንም ፤

እንዲሁም የካህናት ማሠልጠኛ ት ቤት ያስፈልገናል፡ በተጨማሪም በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ከ20 እስከ 30 ካህናት ይገኛሉ ታዲያ እነዚህን አሰልጥኖ በሥራ ላይ ለማዋል የማሠልጠኛ ት ቤት እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው ።

ስለዚህ ለሚመለከተው ክፍል በማቅረብ ርዳታ እንድናገኝና እራሳችንን ለመቻል እንድንበቃ ትብብራችሁን እንጠይቃለን።

አባ ኃይለ ማርያም ካሣ

● አባ ኃይለ ማርያም ካሣ ለኛ የጻፉትን ደብዳቤ ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ቢጽፉ ላቸው የተሻለ ይመስለናል ምክንያቱም እያንዳንዱ ሊቀ ጳጳስ በስብከተ ሀገሩ ላሉት ካህናትና አብያተ ክርስቲያናት መሪና አስተዳዳሪ ነውና ጥያቄውም በርዳታ ሰጮች ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው በስብከተ ሀገሩ በሚገኙ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች በኩል ሲቀርብ መሆኑ አያጠራጥርም።

ስለሆነም ጥያቄውን የሚመለከታቸው ክፍሎች እንዲመለከቱልዎ በመጽሔታችን አውጥተነዋል ።

★★★

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ የከበረ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ።
ከዚህ ቀጥዬ የማሳስብህ የዘመኑ ወጣት፡- በመንገድ ስሄድ "አብደላ" እያሉ ይሰድቡኛል ስለ እግዚአብሔር ታስተምረኛለህ ግን እግዚአብሔርን መቼ አየኸው? በማለት ይዘብቱኛል ። በመጽሐፍ ቅዱስ ለማስረዳት ስሞክርም መጽሐፍ ቅዱስ በሰዎች ተጽፎአልና በቂ ማስረጃ ሊሆን አይችልም ይሉኛል። ስለዚህ ምን ማድረግ ይሻለኛል?

ዲያቆን ተስፋ ማርያም መርዓዊ
ከቅዱስ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን
አዲስ አበባ

● ዲያቆን ተስፋ ማርያም ፡-ሰዎች "አብደላ" ቢሉህ አትበሳጭ፣ አብደላ ስድብ አይደለም አብደላ ማለት በዐረብኛ ገብረ አምላክ የአምላክ አገልጋይ ማለት ነውና ። ስለእግዚአብሔር ህላዌ ለሚከራከሩህም በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረዳትህ መልካም ነው።መጽሐፍ ቅዱስን ከማይቀበሉ ጋርግን አትከራከር ፤ ብትችል የእነርሱ እውቀት ምን እንደሆነ መርምርና በራሳቸው የዕውቀት መጽሐፍ ብትነጋገር ስለ እግዚአብሔር ህላዌ በቂ ማስረጃ ማግኘት ትችላለህ ።

★★★

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በቅድሚያ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ።
በትንቢተ ሕዝቅኤል 38፣2—6፣ ላይ እንደዚሁም በትንቢተ ኢሳይያስ 10፣ 9—10 የሚገኙት ስሞች የሰው የሀገር ወይም የቦታ ስሞች ናቸው ? ከሆኑ በየትኛው ክፍለ ሀገር ይገኛሉ ?

ተክሌ ፈቃዱ
አዲስ አበባ

አቶ ተክሌ ፈቃዱ እነዚህን ስሞች ምን እንደሆኑ ዘርዝረን ለማውጣት ብዙ ገጽ ይወስዳል ፤ ስለዚህ በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ስለተዘጋጀ በየፊደላቸው በዚያ እንዲመለከቱ እናሳስብዎአለን። ዲክሼኔሪው (መዝገበ ቃላት) የሚገኘው በየም

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ርዕሰ አንቀጽ

## ለምን አንድ አይሆንም ?

በዓለም ያለች ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ አንዲት ስትሆን በሥርዐት ተለያይታ ኖራለች እስካሁንም የመለያየቱ በር አልጠበበም የሥርዐት ልዩነት ባህልና ልማድን ሌላውንም ቅድመ ክርስትና የነበረውን ትውፊታዊ ትምህርት ስለሚመለከት ልንጨነቅበት አያስፈልግም። ነገር ግን ብዙዎች ክርስትያኖችን ሲያሳዝን የኖረ አንድ የመለያየት ሁኔታ አለ ። ይኸውም በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል ያለው ልዩነት ነው። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ብሉያት 46

ሐዲሳት 35 በድምሩ 81 ናቸው የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚከተሉትን ትቀበላለች

ብሉያት 49

ሐዲሳት 27 | ድምር 76

ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ከዚህ የተለየ የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር አላት ይህም እንደዚህ ነው ።

ብሉያት 46

ሐዲሳት 27 በድምር 73 ናቸው ።

የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስትያናት ግን ከላይ ከተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት አቆጣጠር በጣም ዝቅተኛ የሆነ የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር አላቸው ለምሳሌ ብሉያት 39 ሐዲሳት 27 በድምሩ 66 መጻሕፍትን ይቀበላሉ ።

በዓለም የታወቁ የታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት የቅዱሳት መጻሕፍትን አቆጣጠር ተናገርን እንጂ ሌሎችም የተለየ ቁጥር ይኖራቸው ይሆናል ።

ቅዱሳት መጻሕፍት በእግዚአብሔር መንፈስ እንደተጻፉ ክርስቲያኖች ሁሉ ያምናሉ ። ነገር ግን በዚህ ልዩነት መሠረት አንደኛው ክፍል ራሱ ከሚቀበላቸው መጻሕፍት በቀር ሌሎችን በእግዚአብሔር መንፈስ እንዳልተጻፉ ይቆጥር ይሆናል ። ይህም በእግዚአብሔር መንፈስ ላይ ብላስፈሚ ዕርፍተ መለከት እንደማድረግ ይቆጠ ራል ። ይህ እንዳይሆን ክርስቲያኖች በክርስቶስ አንድ እንደሆኑ ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍትም አንድ ይሆኑ ዘንድ ያስፈልጋል ።

ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎችን ሁሉ ክርስትናን ለመቀበል ከሚያስቸግራቸው ነገሮች አንዱ በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል ያለው ልዩነት ነው አንድ ክርስቶስን ለመስበክ አንድ አይነት ቅዱስ መጽሐፍ ቢኖር የልዩነት በር እንደሚጠብ እንገምታለን ። ይህ ልዩነት ተወግዶ አንድነት ሊመሠረት የሚችለው በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ጥረት ሳይሆን የዓለም አብያተ ክርስቲያናትን ትጋት ይጠይቃል ። ከዚህም ጋር አንደኛው ክፍል የራሱ ቅዱስ መጽሐፍ ትክክል እንደሆነ ሲገመት የሌላው ቅዱስ መጽሐፍ ትክክል እንዳይደለ ያወራል ይህም ድርጊት የአንድነትን በር ፈጽሞ የሚያጠብ ስለሆነ ትክክል ያልሆነው ትክክል እንዲሆን ፣ ጉዶሎውም እንዲሞላ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ለምን አንድ አይሆኑም ?



# ዓሣ ከባህር ከወጣ ነፍሱን አጣ

የዓሣ ሰፊ ዓለሙ ባህር ቤቱ ነው ። ውቅያኖስ ሀገሩ ነው ። ኻሪቶች መዝናኛዎቹ መናፈሻዎቹ ናቸው። ከዚህ ክልል ውጭ ዓሣ ሀገር የለውም ቤት የለውም የመዝናኛ ሥፍራዎች አያገኝም ሳይቸገረው ሳይጠበው ሰፊውን ውቅያኖስ ትቶ በሌላ ሥፍራ መኖርን ካሰበ በገዛ እጁ ለመሞት ነው ። ሳይጠማው ሳይበርደው ሳይርበው ዓሣ ከባህር ከወጣ ነፍሱን አጣ ማለት ነው ።

ኢትዮጵያዊው ደራሲ "አርሙኝ" በተባለው የሊቅ ድርሰታቸው ውስጥ የማይታረመውን ሃሳብ ለትምህርት እንዲሆነን ብለው በዚህ መልክ አቅርበውታል ።

እጠቅሳለሁ። "ከእለታት አንድ ቀን ዓሣ ለማጥመድ ወደ ወንዝ ወረድኩ ። ከዚያም ስደርስ በመንጠቆ ላይ ጉንጭ አትመላ ቁራጭ ሥጋ በመንጠቆው ላይ አድርጌ ወደ ባሕሩ ወረወርኩት አሳው እወጥመድ ውስጥ እስከገባ ድረስ ከባሕሩ ዳር ቁጭ አልኩ አሉ ። ባጋጣሚው ግን ከባሕሩ አዳራሽ አንድ ከፍተኛ ትርዒት ተመለከትኩ ይኸውም ትንሽቱ አሣ ለመኖር ከእርሷ ያነሰውን ዓሣ ስትውጥ አየሁ ። ይህችኛዋን ደግሞ ከእርሷ ከፍ ያለው አሣ ወዲያውኑ ሲውጣት አየሁ። ይህኛውን ደግሞ ከርሱ ከፍያለው አሁንም ከዚያው ዓይኔ እያየ ዋጠው ። ይህን ትልቁን ደግሞ ከእርሱ የበለጠውን ውጦ ዞር ቢል የኔን መንጠቆ ላይ ሥጋ አፍ አትሞላ በላሁ ሲል ተበላ ። ከሰፊው የባሕር ቤቱ ውስጥ ብዙ የሚበላ እያለ አይጠቀመው ዋጥኩ ሲል ከባሕር ቤቱ ዓሣ ወጣ ወዲያውም ነፍሱን አጣ ።

በጊዜው እኔው ተረድቼው የነበረው ዓሣ ከባሕሩ ቤት ውስጥ ሲኖር እርስ በርስ እየተዋዋጠ ኑሯል፣ ለካስ እኔም ሌላው የዚህ ዓለም ዓሣ ሁኜ በቴን በምድሪቱ ላይ ሠርቼ በአየር ውቅያኖስ ውስጥ እራሴን እንዳኖርኩ ተገነዘብኩ አሳው እርስ በእርሱ ተዋዋጠ ያልኩትም ከንቱ ሆኖ አገኘሁት። ምክንያቱም እኔም ከወንዝ የወረድኩት ሁለቱን አሳዎች የዋጠውን ዓሣ እኔ በቁራጭ ሥጋ አታልዬ ልውጠው ኑሯል። እኔን ደግሞ ሞት ከበስተ ኋላዬ በሞት መንጠቆ ላይ ገንዘብ እንጠልጥሎ ካለሁበት የሕግ አለም ባሕር ቤቴ በገንዘብ ወዳድነት ለራሴ ተድላ ብዬ ሌሎችን እያስጨነቅሁ ገንዘብ አከማቻለሁ ስል ሞት ከዚህች ዓለም ሊወስደኝ እንዳለ አየሁ" ብለዋል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ረቂቅ ምሳሌ ሰው ከእግዚአብሔር የሕግ ባሕር ከህቅና ከእውነት ውቅያኖስ ውስጥ ራሱን አውጥቶ ባለመታዘዝ በማጭበርበር በንጥቂያ ልኑር የሚል ከሆነ ከእውነት የሞት ባሕር ወጥቶ ጥርጊያውን ለሞት ያዘጋጃል ሞት የምንለውም የሥጋውን ብቻ ሳይሆን በቁም የሞራል ሞት አለ ቢያልፍም የታሪክ ሞት አለበት ይህም በዘር በትውልድ እየተላለፈ ይጉዳል።

ከሁሉም በላይ ዘላለማዊ ሞት አለ ከሥጋ ጋር አብራ ጨቋኝና በዝበኟ ዋሾና አጭበርባሪ ሁና የሰነበተችውም ነፍስ ቅጣቷን በገሃነም ወህኒ ታገኛዋለች። ምነው ቢባል ከሕግ የባሕር ክልል ውስጥ ወጥቶ ሥጋ ለራሱ ሲያግበሰብስ እርሷም ድርሻዬን ስንቄን በማለት ከሥላሴ ሣጥን ውስጥ የምታኖረው ብዙ ነበራት። ግን በለዘብተኝነት ከምዕዋት ኩሬ ውስጥ ወጥታ ንፉግ ሥጋ ራሱን ወዳድ ገብጋባ ሥጋ የጽድቅ ምንጪ ሲያደርቅባት ዳር ቆማ በማየቷ ሲያደፈርሰው ዝም ብላ በመመልከቷ የዚህ ዓለም ጠም አዳሪዎች የሚበሉት ሲያጡ እርሷ ቅቤ ስታቀልጥ የሚጠጡት ሲያጡ ወይን ስትጠምቅ ከሥጋ ጋር ባደረገችው አድሃሪ ሥራዋ ፍርድ በሰማያት እንዳለባት ታላቁ ወንጌል በአራቱ ሐቀኛ ወንጌላውያን ምስክሮች በማቴዎስ በማርቆስና በዮሐንስ ተመስክሮበታል።

ዓለማችን ከተፈጠረ ጀምሮ የሰው ልጅ ከግለሰብ ወደ ቤተሰብ ከቤተሰብ ወደ ማኅበራዊ ኑሮ ራሱን ባሸጋገረ ቁጥር በየዘመናቱ ከሕግ ባሕር በወጣ ቁጥር እንደአሳው ነፍሱን እያጣ ከዚህ ለመድረሱ የታሪክ መዛግብት ይመሰክሩበታል ከዚያም በላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በማተሚያ መሣሪያ ከነማንም መጻሕፍት ቀድሞ የታተመው አሁንም ዓለምን በሙሉ በማጥለቅለቅ ምላስ ከምታክል ደሴት ሳትቀር ለምስክርነት ተወዳዳሪ በማይገኝለት ብዛት የታተመውን ወንጌል የምሥራቹን ጆሮ ያለው ይስማ ፣ ድንጋይ ተብለህ እንዳትጣልጨው ሁነህ ሁሉን አጣፍጥ በማለት ለአለንበት ዓለም ኰረጥ ያለ ሥራ አንድ ናበረከት ያስተምራል።ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ ሂዱና ዓለምን ሁሉ አስተምሩ በማለት በድንቁርና ጨለማ ውስጥ የተጣሉ ወገኖቻችንን እንድናስተምር ታዘናል። መብራታችሁን አብርታችሁ ከእንቅብ በታች ሳይሆን ከእንቅብ በላይ ታኖሩታላችሁ ። በተራራ ላይ የተሠራች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም ሲል እኛ ወንጌልን ከማስተማር ወደኋላ ቀርተናል፣ ፣ይህ ታዲያ ከሕግ ባህር ውስጥ መውጣት አይሆንም ? እንደ ዓሣው ነፍስ ማጣት አይሆንም? በሕይወት እንድንኖር ወንጌሉን እናስተምር። ብርሃኑ ለሁሉም እንዲያበራ ሁሉን ሀ ሁ እናስቆጥር ትእዛዙ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ ይለናልና።

ያሬድ አስቻለው



www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፡ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፡ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።




አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ

ስልክ ቁጥር 11-66-16

የፖ.ሣ.ቁ. 31-37

አዲስ አበባ


የ19 ዓመት ወጣት ነኝ ፤ በዚህ እድሜዬ ሲጋራ እጨሳለሁ ለመተው ብሞክርም አካባቢው ሊያስተወኝ አልቻለም ችግረኛ ስለሆንሁ የቀን ሥራ ሠርቼ የዕለት ራቴን ለማገኘት ስዟዟር በመንፈሳዊ አካባቢ ስለ ማልውል ሲጋራውን ለመተው አልቻልኩም፤

ስለዚህ 1ኛ ሲጋራ ማጨስ ኃጢአት ነውን? ሲጋራ ማጨስ ኃጢአት መሆኑን የሚገልጽ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለ ቢያስረዱኝ፤

2ኛ ሲጋራ በማጨስ ብቻ የወንጌል ትምህርትን ከመማርና ከማስተማር መከልከል ይናርብኛልን?

3ኛ ለወደፊት የወንጌል ሰባኪ ሐዋርያ ለመሆን ዓላማ አለኝ ስለዚህ ምክርህን ብትለግሰኝ።

ደስታ ዓለሙ

ከመ ቱ ቅዱስ ሚካኤል መንፈሳዊ ማኅበር

ወጣት ደስታ ዓለሙ ጥያቄህን ተመልክተነዋል በመሠረቱ ሲጋራ ማጨስ በማንኛውም መንገድ ቢሆን ጉዳት እንጂ ጥቅም እንደሌለው የጤና ባለሙያዎችና ሌሎችም ሊቃውንት ያስረዳሉ፤ ይሄውም ሲጋራ 1ኛ ለሳንባ ነቀርሳ መነሻ ይሆናል 2ኛ ልብ በሚገባ ሥራውን እንዳያከናውን ያደርጋል ሲሉ የጤና ሊቃውንት ያስረዳሉ።

በኢኮኖሚ (በምጣኔ ሀብትም) በኩል ከፍተኛ ውድቀት እንደሚያመጣ ግልጥ ነው ችግረኛነትህንም ያባባሰው ይኸው ሊሆን ስለሚችል ሲጋራውን ፈጽመህ ለመተው ሞክር፤

ሲጋራ ማጨስ ኃጢአት መሆኑን የሚገልጽ በመጽሐፍ ቅዱስ የለም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ሁሉ ተፈቅዶልኛል ሁሉ ግን አይጠቅምም፤ ሁሉ ተፈቅዶልኛል በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳን አይሠለጥንብኝም" ብሏል 1ኛ ቆሮ. 6፡12 ከጥያቄህ እንደተረዳነው አንተ በሲጋራ ሱስ እንደተጠመድህ ግልጽ ነው ኃጢአት የማይሆነውና ለሰዎች የተፈቀደው ሁሉ በሰዎች ላይ በሱስነት ሊሰለጥን አይገባውም ስለዚህ ሲጋራውን ፈጽመህ መተው ይኖርብሃል ፤ ከጉዳት በቀር ጥቅም የለውምና ችግረኛነትህንም ያባባሰብህ ይኸው የሲጋራ ሱስ ሳይሆን አይቀርም በሌላ በኩል ግን በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23 ላይ አእምሮ የሚያቃውሱትንና ሱስ የሚያመጡትን ዕፅዋት ሁሉ መብላት እንደማይገባ ተወስኖአል።

ሲጋራ በማጨስ የወንጌልን ትምህርት ከመማርና ከማስተማር መከልከል አይኖርብህም ፤ ግን ሲጋራ ማጨስ በሰዎች ዘንድ እንደሚያስነቅፍህ እያሰብህ የሕሊና ወቀሳ አሳድሮብሃል ፤ ስለዚህ የሕሊና ወቀሳ የሚያሳድርብህን ለማረም ቻል ።

የወንጌል ሰባኪ ለመሆን ከሁሉ አስቀድሞ በሕገ ወንጌል መጽናትና ጎጂ የሆኑትን ልማዶች ሁሉ ከራስ ማስወገድ ያስፈልጋል። ስለዚህ አንተም ሲጋራ የማጨስ ልማድህን አስወግድ የማይጠቅም የሚጎዳ ልማድ ነውና ከዚህም ጋር ሌላ የማይጠቅም ልማድ ከአለብህ አስወግደህ ራስህን በክርስቲያናዊ ሥራ አስተካክል ለዚህም እግዚአብሔርን በጸሎት ጠይቅ ዓላማህ መልካም ስለሆነ የለመኑትን የማይነሣ፤ የነገሩትን የማይረሳ እግዚአብሔር እንደሚረዳህ እናምናለን።





# የኢትዮጵያውያን ቀደምትነት በተቀደሱ ቦታዎች

ዴር ሡልጣን

ከአለፈው የቀጠለ ክፍል 5

የመዝገብ ቁጥር 151 ገጽ 91 /ስጅል 151 ሳፍሐ 9/ ከኢየሩሳሌም ላይ መሐከማ ሽር ኢያ ከሚባለው /የአስተዳደር ፍርድ ቤት/የግሪክ ክርስቲያን ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ ባስልዮስ የተባሉት ሊቀ ጳጳሳት በኢየሩሳሌም ላይ የሚኖሩ ዘያአል ቃኢዳ በተባለው ወር 10 ቀን 1064 ዓመተ ሒጅሪ የተጻፈ የመንግሥቱ አዋጅ ያለበት ማስረጃ በእጃቸው ይዘው ከዋናው ኃላፊ ኢየሩሳሌም ላይ ከሚገኙ ቀዲ የመሐከማ ሽርኢየ /ፍርድ ቤት/ ዋና ዳኛ ከአብደል ራሂም ዘንድ ቀረቡ ።ከዚያም አዋጅ ጋር ለኢየሩሳሌም ዋና ቃዲ የተላከ ደብዳቤ ቀጥሎ የሚዘረዘረውን ጽሑፍ የያዘ ማስረጃ ይዞ ቀርቧል። በግሪክ ኦርቶዶክስ ማኅበር ሊቀ ጳጳሳት ውስጥ የሚተዳደሩ እንዲሁም የኢትዮጵያን ንብረቶች ለመጠበቅ ፈቃድ ያላቸው የግሪክ ኦርቶዶክስ ፓትርያሪክ በቦታው ላይ እንዲሁም ኢየሩሳሌም ላይ የሚኖሩ ከኢትዮጵያውያን ማኅበር ላይ የሚገኘው ርስትና ቦታ ማንኛውንም ለመጠበቅ መብት አለው። ማንኛውም የክርስቲያን ማኅበር የሆኑ ሁሉ ኢየሩሳሌም ላይ በኢትዮጵያ ንብረቶችና ሥፍራዎች ውስጥ እንዲገባ ፓትርያርኩ ለማንም ቢሆን አይፈቅድም። ይህ በመንግሥት የተሠራው ደንብ አዋጅ ከመንግሥቱ መዝገብ እንዲመዘገብልኝ ሲል የግሪክ ሊቀ ጳጳሳት የጠየቀና የንጉሡ ትእዛዝ ከተነበበ በኋላ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ግሪክን መስለው ይኖራሉና የግሪክ ሊቀ ጳጳሳትም የኢትዮጵያውያንን ርስት ለመጠበቅ መብት አለው። ወይም በርሱ በኩል እንዲጠበቅ የሚፈቅድለትም ቢሆን ይጠብቃል። የተጠቀሰውም ፓትርያርኩ በኢየሩሳሌም የሚገኝ ማንኛውም ክርስቲያን በኢትዮጵያውያን ርስትና መብት እንዳይገባ የሚከለክለውን የንጉሡን አዋጅ በመዝገብ ቤት አስመዝግቦ ከላይ የተጠቀሰው ባስልዮስ የተባለው ሊቀ ጳጳሳት በኢየሩሳሌም የሚገኙትን አርመኖች እንዲቀርቡልኝ ሲል ክስ አቀረበ እነርሱም በኢትዮጵያውያን ርስቶችና መብቶች በገዳማቸውም ዑደት በሚያውዱበትም በቤተ ክርስቲያናቸውም ላይ ባልሆነ እጃቸውን የጣሉ ናቸው። በጎልጎታ ውስጥና በውጭም ከሚገኙ የኢትዮጵያውያን ርስት እጃቸውን ያነሡ ዘንድ ትእዛዝ እንዲሰጥና እንደ ንጉሡም ትእዛዝ እንዲያስረክቡኝ ሲል ክሱን ቀጠለ ከላይ የተጠቀሱትም የሕግ መሪ አገረ ገዥ ሐኪም አል ሽርኢ ከአርመን ሊቀ ጳጳሳት ወኪል ደኒክና ያዕቆብ ከተባለው ትርጁማን ጋር ሁሉንም ሰብስቦ ካቀረበ በኋላ የንጉሡን ትእዛዝ አነበበላቸው ፡ ትእዛዙም በንጉሡ ፊርማና ማኅተም የተከበረ ነው። ቃሉንም አስታወቃቸው እንዲህ ሲል ኢትዮጵያውያን የግሪክ ሊቀ ጳጳሳት መስል ናቸው። እሱም በርስታቸውና በመብታቸው ሁሉ እንዲጠብቅ መብት አለው። ይኸውም በኢየሩሳሌም ከሚገኙት ክርስቲያኖች ሁሉ አንድ እንዳይገባባቸው ክልክል ለመሆኑ በሕገ መንግሥት ታውቋል። አርመኖች ሕግ ባልሆነ እጅ ያደረጉትን የኢትዮጵያውያንን ርስትና መብት ለግሪኮች እንዲያስረክቡ አዘዛቸው። ለሐበሾች በእጃቸው የነበረውን ሁሉ ገንዘባቸውን ቀንዲላቸውንም መጻሕፍቶቻቸውንና መስቀሎቻቸውንም በተለይም በእነሱ ስም የተጠራ ሁሉ የሚጸልዩበትም የሚያውዱበትም በጎልጎታ ውስጥና በውጭም ያለ ገዳማቸውንና ርስታቸውንም ይህንን የመሳሰለ ሥራ ሁሉ በሕገ መንግሥቱ መሠረት ከላይ እንደታዘዘው በንጉሡ ትእዛዝ አስረክቡ አላቸው። ከላይ የተጠቀሱትም የአርመን ኃላፊዎች የንጉሡን ትእዛዝ በፍርድ በትሕትና ተቀበሉ ከዚህም በኋላ አስተዳዳሪው ይህን ቦታ ከአርመኖች ወደ ግሪኮች ለማረካከብ የቦታች ባለሥልጣናችን አዘዘ። የእስላሞች የዳኞች ዳኛ ሰላህ አፈፍ የኢየሩሳሌም አስተዳዳሪ የሕግ መሪ ምክትልና የተከበሩም እብራሂም አታ የተከበሩም የደማስቆ ገዥ አትክዳ የተባሉትም ሁነው ከእነሱ ጋር ብዙ የእስላሞች ሕዝብ ተከትለዋቸው በጎልጎታ ውስጥ ከኢትዮጵያውያን ርስትና መብት ላይ ደረሱ ። ከዚያም በኋላም ኢብራሂም የተባለ የግሪክ ትርጁማን ሰርኪስ የሚባልና ከአርመኖችም ሁሉ የሐበሻ ርስት ተረከበ ። በተለይም ኢትዮጵያውያን የሚጸልዩበት በስማቸው የታወቀ ነው። ይሄውም እንደሚከተለው ነው።ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከመስቀል አውርደው አጥበው ከገነዙበት ላይ 8 ቀንዲሎች ተሰቅለው ከሚበሩበት የጌታችን ትንሣኤ ዕለት ብርሃን ከሚወጣበት ውስጥ ቀጥሎም እሱ ውስጥ ከሚገኘው ቤት ይሄውም ቅዱስ መቃብር ነው ደግሞ ብርሃን ከሚወጣበት ቤት በስተውጭው ሁለት ቀንዲሎች የሚሰቀሉበትአንዱ በደቡብ በኩል ሁለተኛው በሰሜን በኩል ነው። በምህዋሩ የሚገኙ 3 ክፍል ቤቶች በዚሁ በተጠቀሰው ቤ/ ክርስቲያን በስተደቡብ በኩል ያለ በተለይ የሐበሻ ነው።ከዚህም ላይ በኢትዮጵያውያን የታወቀች ቤተ ክርስትያንና በርሷም ውስጥ የሚገኙ መብራቶችና ፋኖሶች ደግሞ እንደዚሁ በስተሰሜን በኩል ያሉ ሁለት ክፍል ቤቶች ደግሞ በጥጉ የሚገኙ የዕንጨት ጥርብ ቤቶች የነሱ ነው ። ይሄውም በሰሜን በኩል ነው። ደግሞ በስተምሥራቅ በኩል ያለ መቅደስ የሐበሾች መሆኑ ምሥራቅ በኩል ያለ መቅደስ የሐበሾች መሆኑ የታወቀ ነው የዚሁ መቅደስ መልክ በደቡብ እንጨት ነው ። ይህ ከዚህ በላይ የተቆጠረ በተጠቀሰው ቤተ ክርስቲያን በደቡብና በስተምሥራቅ መካከል ያለ መቅደስ በሱም የሚገኙ አልጋዎች በእምዶቹም ላይ ያለ ዑደት የሚያውዱበትና በሱም የሚገኙ የመብራት ፋኖሶች የዚሁም በር መዝጊያው ጥሩ በሆነ ጥርብ ዕንጨት ነው።ይህ ከዚህ በላይ የተቆጠረው ሁሉ በጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው ይህንም በታዘዘው ሕግ መሠረት አረካከቡ። እንደዚሁም በጎልጎታ ውስጥ የነበረ የኢትዮጵያውያን የብር ቀንዲሎችና ሲኒዎችም እንዲሁም የብር መስቀሎች ምንም ስላልተገኙ ግሪኮች ከራሳቸው 8 የብር ቀንዲል አምጥተው ከኢትዮጵያውያን ቀንዲል መስቀያ ላይ ሰቀሉበት ። ይሄውም 7 ቀንዲሎች የትንሣኤ ዕለት ብርሃን ከሚወጣበትና በውስጡም ከሚገኘው ከቅዱስ መቃብር ላይ ነው። አንዱንም ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግንዘት ላይ ሰቀሉት በጎልጎታ ዘግተው የሚኖሩ ሐንስ የተባለ ኢትዮጵያዊና ዮሴፍ የተባለ ሶርያዊ እንዲህ ሲሉ አሳሰቡ ፡ በግንዘቱ ላይ የነበረውን የኢትዮጵያውያን የብር ቀንዲል አርመኖች ወስደውታል። ምክንያቱም ሕግ በመተላለፍ የሐበሾችን መብት እጅ አድርገው ስለነበረ ነው አሉ። ከዚህም በኋላ በጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረው ከታየና ካረካከቡ በኋላ በውጭ ከጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን የተያያዘ በስተደቡብ በኩል ከምድር ቤት የሚገኘውን የኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያን በሩም ወደ ደቡብ የሆነ ግሪኮች ከአርመኖች እጅ ተረከቡ፤ ቀጥሎም የኢትዮጵያውያን ገዳም ተረከቡ። የዚህም ገዳም በር መንገዱ በጎልጎታ በር አደባባይ ነው። በዚሁም ገዳም በዙሪያው የሚገኘው ሁሉ መኖሪያውንና ቤቶቹንም ሁሉ ደግሞም ከፍተኛው ቤተ ክርስቲያን ከውስጡ የሚገኘውም ሁሉ በዚሁ በተጠቀሰው ገዳም ነው ደግሞም የመሥዋዕት መሥሪያ ቤት (ቤተ ልሔም) በሱም ውስጥ የሚገኘው ደግሞ የካህናቱ አልባሳት ማኖሪያ ትልቅ የተቆለፈ ሳንዱቅ በሱም ውስጥ የሚገኘው ብዙ የሐበሾች ቋንቋ መጻሕፍት (6 ትናንሾች የብር ጽዋዕ ፤ የብር ጽንሐሕ፤ 4 የብር

ወደ ገጽ ፲ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የሃይማኖት ዐምድ

«ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፡ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፡፫) ።

## ምሥጢረ ሥላሴ

### 2ኛ አንድነት በሦስትነት

"ሥላሴ በባህርይ በመለኮት''በአምላክነት አንድ ናቸው። ሊቁ አትናቴዎስ አብ አምላክ ነው ወልድ አምላክ ነው ። መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው ። እንዲህ ስለተባሉ ግን ሦስት አማልክት አይባሉም። በማለት በስም በግብር በአካል ሦስትነት ሲኖራቸው በባሕርይ በመለኮትና በመንግሥት አንድ መሆናቸውን አመልክቶአል።

በፈቃድና በባሕርይ አንድ የመሆናቸው ምሥጢር አካል በአካል ህልው ሆና በአንድ ልቦናነት በአንድ ቃልነት በአንድ እስትንፋስነት መኖራቸውን ይገልጣል ።

ይህም ማለት አብ በፍጹም አካሉ ልብ ስለሆነ ሌላ ልብ የለውም፣ ወልድም በፍጹም አካሉ ቃል ነው፣ ሌላ ቃል የለውም፣ መንፈስ ቅዱስ በፍጹም ገጹ በፍጹም አካሉ እስትንፋስ ነው ሌላ እስትንፋስ የለውም በማለት ቴዎዶጦስ ፣ ጐርጎሬዎስና ዲዮናስዮስ በየተራ ገልጸውታል።

ታዲያ አብ በልቦናነቱ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ህልው ነው፡— ወልድም በቃልነቱ በአብ በመንፈስ ቅዱስ ህልው ሲሆን መንፈስ ቅዱስም በእስትንፋስነቱ በአብ በወልድ ህልው ነው ተብሎ ተጽፏአል። ፊላታዎስ ዘእስክንድርያ ክፍል 2 ይህም ማለት ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ አብ ልቦናቸው ነው፣ ለመንፈስ ቅዱስና ለአብ ወልድ ቃላቸው ሲሆን ለአብና ለወልድ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋሳቸው ስለሆነ በአብ ልቦናነት ሦስቱም ያስባሉ በወልድ ቃልነት ሦስቱም ይናገራሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ሦስቱም ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ። በጠቅላላ ይገነዘባሉ ማለት ነው ። ስለዚህ ነው ሥላሴ በአብ ለባውያን በወልድ ነባብያን በመንፈስ ቅዱስ ሕያዋን ተብለው የሚጠሩት።

እንደዚህ ባለው መገነዛዘብ ቃልና እስትንፋስ ከልብ መቋረጥ እንደሌለባቸው ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ መለየት የለባቸውም በፈቃድ አንድ እንደመሆናቸው በአምላክነት ሥራ ሁሉ አንድ ሆነው ይሠራሉ ይፈጽማሉ፣ ሲል ሲራኮስ ዘአንጾክያ ተናግሮአል ።

አባ ሕርያቆስም አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ያስባሉ፣ ይናገራሉ፣ ይፈቅዳሉ ወዘተ በማለት የፈቃድ አንድነታቸውን አሳይቷል።

ሦስቱም እሳት ይባላሉ ነገር ግን አንድ እሳት እንጂ ሦስት እሳት አይባሉም ባጠቃላይ እንዲህ ባለ ምልአት ስፋት ርቀት እንዲህም ባለ አንድነት ሦስትነት ሳይወሰኑ አንዱም ከሌላው መቅደምና መቀዳደም ሳይኖርባቸው አንዱም ለሌላው ተገዥ ሳይሆን በአካል ፣ ሆነንም በግብር ሦስት በፈቃድ በህልውና በአምላክነት አንድነትን ገንዘብ አድርገው ቅድመ ዓለም የነበሩ ሥላሴ ዛሬም አሉ ወደፊትም ይኖራሉ'' ሲል ሳዊሮስ ወደ አንስጣስዮስ በጻፈው መልእክት ክፍል 1 ተናግሮአል።

ታዲያ በሥላሴ አንድነት ካለ ብሎ ሦስትነትን ሦስትነትምካለብሎአንድነትን ሊያፈርስ ወይም ሊቀንስ የሚችል ከቶ የለም። የክርስቲያን እምነትና ትምህርት ይኸን የተደገፈና በዚህም የጸና ነው'' ተብሎ ተጽፎአል።

1ኛ ስለ እግዚአብሔር አብ

''ከሦስቱ አካላት አንዱ አብ ሲሆን ትርጉሙ አባት ማለት ነው ምክንያቱም ወልድን ያለእናት ይወልዳል። መንፈስ ቅዱስንም ያሠርዕልና ነው ።

እንዲህ ስለ ተባለ ግን ወልድንና መንፈስ ቅዱስን በዘመን አይቀድማቸውም አይበልጣቸውም ቅድምናቸው አንዲት ናት ሲል ጎርጎሪዎስ ገባሬ መንክራት በክፍል 1 ጽፎአል። ይህም ማለት አብ የነበረበት ወልድና መንፈስ ቅዱስ ያልነበሩበት ጊዜ ከቶ የለም አብ ቀዳማዊ አምላክ እንደሆነ ወልድ ቀዳማዊ አምላክ ነው ። መንፈስ ቅዱስም ቀዳማዊ አምላክ ነው። እንዲህም ስለተባለ ሦስት አማልክት አይባሉም አንድ አምላክ እንጂ። ስለዚህም ነበር 318 ሊቃውንት "በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን እርሱም ዓለምን ሁሉ የሚገዛ የሰማይና የምድር ፈጣሪ የሚታየውም የማይታየውም ሁሉ በርሱ የሆነ የተፈጠረ" ሲሉ የተናገሩትና በውሳኔ ያጸኑት ።

ቄስ መክብብ አጥናው

---

## የኢትዮጵያውያን ቀደምትነት...

ከገጽ ፭ የዞረ

ኩባያዎች 10 የብር መንካዎች፣ ነጭ ስምንት ትልልቅ ደግሞ ትናንሽ የብር መስቀሎች ደግሞ የንኬል መስቀሎችና አንድ ነሐስ 7 ትልልቅና 7 ትንንሽ የብር መስቀሎችና አንድ የነሐስ መስቀል 1 ወንጌል ገበታው በብር የተለበጠ ትንሽ ምንጣፍ የብር ቀንዲል ከሐበሾች የመስዋዕት ቤት የተሰቀለ 1 ትልቅ በራድ ይሄውም በቁርባኑ ቤት ነው /ቤተ ልሔም/ደግሞ ትልቅ የነሐስ ገበታና ትንሽ የነሐስ ሲኒ የብረት ዓይነት የዕቃ መስቀያ የብረት መጥረጊያ የነሐስ ሽመዳን የመብራት ማቆሚያ ትንሽ የብረት ወንበር 5 የነሐስ ሽመዳኖች። በምድር ቤት ከሚገኘው ክፍል የተገኙ ከነሐስ የተሠሩ ዕቃዎች የወጥ መሥሪያ ድስት ዋንጫ፣ የልብስ ማጠብያ ፣ ዳካዎች ሙቀጫና ዘነዘና፣ 3በራዶች ባለመክደኛ የመስዋዕት ማሥመሪያ ሽመዳን ይህ ሁሉ በሐበሾች ገዳም ተገኘ። ከዚህ በስተቀር ሌላ አልተገኘም ከዚህ በላይ የተቆጠረውን ግሪኮች በታዘዘው ሕግ መሠረት ከአርመኖች እጅ ተረከቡ አስተዳዳሪውም ይህንኑ በጽሑፋቸው ስለ አረጋገጡ ከብራቸውን ያኑርልን አርመኖችም ከኢትዮጵያውያን ርስትና መብት ፈጽመው እንዲለቀቁ አደረጉ።ሁለተኛም ግሪኮች በኢትዮጵያውያን ርስትና መብት ምክንያት በሚያውዱበትም በገንዘባቸውም ሆነ እንዳይቃወሙ አስጠንቀቋቸው ይህም ሕግ ንጉ

ወደ ገጽ ፱ የዞረ



# አስተያየት ከአንባቢዎቻችን

በቁጥር 21ና 23 ትንሣኤ መጽሔት ሁለት ሰዎች ስለዐሥራት አስተዋጽኦ የሰጡትን ሀሳብ ተመልክቻለሁ ፣ በሃሳቡም ስለተደሰትኩበት ስለአሥራት አስተዋጽኦ እግዚአብሔር ምን እንደሚል ከቅዱስ መጽሐፍ ለትንሣኤ መጽሔት ተከታታዮች በአጭሩ ልጠቁም እወዳለሁ ። አብርሃም በግፍ የተወሰደበትን የሎጥን ሀብት ከነገሥታት ማርኮ ሲመለስ የልዑል እግዚአብሔር ካህን ለነበረው መልከጼዴቅ ከአለው ሁሉ አሥራትን ሰጠው ። (ዘፍ. 14፡17-20) ስለዚህ አብርሃም በሕገ-ልቡና ተመርቶ "አሥራትን" ለእግዚአብሔር ክብር በመስጠት የመጀመሪያው እንደሆነ ከቅዱስ መጽሐፍ እንመለከታለን ።

በሕገ-ኦሪትም "አሥራት እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ለእስራኤል ልጆች ሙሴን ካዘዘው ትእዛዛት አንዱ እንደሆነ በዘኁ. 27፡30-34 ተገልጾአል ። በጠቅላላው ሰዎች ከአብርሃም ጀምረው በሙሉ ፈቃደኝነት "አሥራትን" ለአምላካቸው ይሰጡ እንደነበር ከቅዱስ መጽሐፍ እንረዳለን ። ዘፍ. 28፡22 ፣ ዘሌ. 22 ፡ 30-33 ፣ ዘኁል. 18 ፡ 20-28 ፣ ዘዳግ 12፡6. 7. 17-19 ፣ 31 ፡ 5. 7. 12 ፣ ነህ . 10 ፡ 37. 38 ፣ ነህ. 13 ፡ 10-13 ወዘተ. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ጥቅሶች በማስተዋል ብናነባቸው "አሥራትን" በማውጣት በረከትን ከአምላካቸው የተቀበሉትን ሰዎች ታሪክ ከማወቃችንም ሌላ እኛ ክርስቲያኖችም "አሥራትን" ለእግዚአብሔር የመስጠት ግዴታችንን መረዳት እንችላለን ።

በትንቢተ ሚልክያስ በምዕ. 3 ፡ 7-12 ተጽፎ እንደምናገኘው "አስራትን" ያልሰጡ ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ሌባ ተቆጥረው ተወቅሰዋል ። ወቀሳውም፡ "ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል ፣ የሰረቃችሁኝም በአሥራት በበኩራት ነው ። ሲል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ወቅሶአቸዋል ፣ ይህ ወቀሳ በዚያን ጊዜ ለነበሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆን በቃሉ መሠረት እንደሌባ እንደሆንን እናስተውል ፣ ካስተዋልንም ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን በጻፈው መልእክቱ ፡- "የሰረቀ ከእንግዲህ ወዲህ አይስ



አስተያየቱን ያቀረቡልን አቶ ምንውየለት መላክ

ረቅ ፣ ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለጐደለው የሚከፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጆቹ መልካም እየሠራ ይድከም" ይላል ። (ኤፌ. 4፡ 28)

ስለዚህ የአለፈው ጥፋታችን በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ኃጢአት እንደያማይቆጠርብን አምነን ከዚህ ቀደም "አሥራትን" ለቤተ ክርስቲያን በአለመስጠታችን ተጸጽተን ለወደፊት ያለውን በሙሉ ፈቃደኝነት ለመስጠት ከልብ እንነሣ ።

በዘዳ. 8፡17 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር "ጉልበቴ ይህን ሀብት አመጣልኝ እንዳትል" በማለት የአለንን ሁሉ የሰጠን እርሱ እንደሆነ ይናገራል ።

በዘዳ. 8፡18 "ሀብት ለማከማቸት እርሱ ጉልበት ስጥቶሃልና አምላክህን እግዚአብሔርን አስብ" በማለት የአለንን ሁሉ በጉልበታችን አገኘነው ብለን እንዳንመካ ያስጠነቅቀናል ። ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮሜ በጻፈው መልእክቱ ፡- "በሕይወት ብንኖርም ፣ ብንሞትም እኛ የጌታ ነን'' ይላል ። እንግዲህ ምን እንላለን እንኳንስ ሀብታችን እኛ የእግዚአብሔር ነን ፤ ነገር ግን አምላካችን "አሥራቱን ወደ ጐተራ አግቡ'' ሲለን ልባችንን እልከኛ አድርገን ከአሥር አንድ ልንሰጥ ፈቃደኞች አልሆንም ። ከአሥር አንድ ለእግዚአብሔር እምቢ ያልን ሁሉ ታምመን በአልጋ ላይ ብንውል ጠቅላላ ደመወዛችን ለእኛ መሆን እንደማይችል እናስተውል ። የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት በማድረግ አሥራትን ለቤ ክ ብንሰጥ በሰዎች አመለካከት ሀብታችን የተቀነሰ ይመስለናል ፣ ነገር ግን "በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን አሥራቱን ሁሉ ወደ ጐተራ አግቡ ፣ የሰማዩንም መስኰት ባልከፍትላችሁ በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ'' ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሚል. 3 ፣ 10 በዚህም ቃል መሠረት ለእግዚአብሔር የሆነውን "አሥራት" ለቤ/ክር ብንሰጥ ቀሪው እንደሚበረክትልን የታመነ ነው ። አምላካችን የሚሳነው ነገር የለም ፣ እንኳንስ ያለውን በማበርከት ቀርቶ ይህን ዓለም ከአለመኖር ወደመኖር ያመጣ ነው ብለን እናምናለን ። በችግር ምክንያት በቤታችን ደስታንና ሰላምን ያጣን ሁሉ የእግዚአብሔርን በረከት ለማግኘት ሊቃሉ እንታዘዝ ።

አሥራትንም ለቤ ክርስቲያናችን ለመስጠት እንነሣ ። ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዛችን ቀሪው ሀብታችን ከመበርከቱ ሌላ ለቤ/ክ የሰጠነው አሥራታችንም በተዘዋዋሪ የሚጠቅመን እኛኑ ነው ። በተለይም ቤ/ክ እራሷን እንድትችል በተጠየቀችበት በአሁኑ ጊዜ በቅዳሴ ለሚያገለግሉት ካህናትና ወንጌልን ለሚያስተምሩ መምህራን ደመወዝ ሊሆን የሚችለው እኛ ክርስቲያኖች ለቤ/ክ የምንሰጠው አሥራት ነው ፣ ስለሆነም የካህናት አገልግሎታቸው የመምህራንም ትምህርታቸው የሚጠቅመን እኛኑ ነው በየዓመት በዓሉ የምንመለከተው ምእመናንን በማጽናናት ፈንታ የሚያስፈራሩ ፣ ወንጌልን በማስተማር ፈንታ የማይጠቅሙ ቃላትን በመደመርደር ገንዘብ የሚሰበስቡ ባህታውያን ነን ባዮች ናቸው ።

ስለዚህ ቤ ክርስቲያናችን እኒህን አታላዮች በሕጋዊ መንገድ አስወግዳ ፡- ለምእመናን ክርስቲያናዊ ሕይወት የሚያስቡ እውነተኞች መምህራንን ከያሉበት ፈልጋ ለስብከተ-ወንጌል ለማሠማራት ፡ በእሷ ትም መምህራን እግር የሚተኩ ሰዎችን ለማፍራትና ምትክ እያጡ በመሄድ ላይ ያሉትን ቅዱሳት መጻሕፍት ለመጠበቅ

አሥራት ያስፈልጋታል ክርስቲያኖች በአሥራት አስተዋጽኦ የራሳቸውን ችግር አስወግደው ዓለምን ሲረዱ ይታያሉ ። እኛ ግን እራሳችንን ለመርዳት አቅቶን ቤ ክርስቲያናችን እየተዳከመች በመሄድ ላይ ትገኛለች በቁጥር 23 የትንሣኤ መጽሔት ላይ የምሥራቅ ጀርመን ቤ ክ 50 ሆስፒታልን ሠርታ ኅብረተሰቡን እንደምታገለግልና 15.000 ሰዎችንም ቀጥራ እንደምታሠራ የተገለጸውን ዜና ያነበበ ሁሉ ኅብረተሰቡን የምታገለግልበት አንድም ክሊኒክ ለሌላት ቤ/ክርስቲያናችን የማይቆረቆር ክርስቲያን እንደማይኖር ተስፋ አለኝ ። ለምሳሌ የምሥራቅ ጀርመን ቤ ክ ካለችበት ደረጃ የደረሰችው ምእመናኗ በሚሰጡት አሥራት አስተዋጽኦ ስለሆነ ሁሉም በየሰበካ ጉባዔው ከዐሥር አንድ ለማዋጣት ጊዜ ሊሰጠው አይገባም እላለሁ።



www.ethiopianorthodox.org

# ይህን ያውቁ ኖረዋል ?

ከእጅጉ ረታ

በየትኛውም የሃይማኖት ክልል ውስ ጥ እንገኝ ፣ የየትኛውም እምነት ተከታ ዮች እንሁን ብዙዎቻችን ጾምን የምናቆ ራኘው ከመንፈሳዊ ሕይወታችን ጋር ብቻ መሆኑ የታወቀ ነው ። ከዚህ ውጭ ጾም የሚሰጠው ጥቅም ይኑር -አይኑር እምብዛም የምንጨነቅበት አይመስል ም ። ነገር ግን እኛ ከምናስበውና ከምና ውቀው በላይ ጾም በሕይወታችን ውስ ጥ የሚሰጠው ጥቅም አለ ። በጤንነታ ችን ፣ በአካል አቋማችን ፣ በአእምሮአ ችን ፣ በአስተሳሰባችን ባጠቃላይ በግ ልም ሆነ በማኅበራዊ ኑሮአችን ሕይ ወት ላይ ጾም ከፍ-ያለ ዋጋ ያለው ጥቅ ም የሚያስገኝ መሆኑ ከታወቀ ዘመናት አልፈዋል ። በዚህ ባለንበት ዘመን ጾም እንደ ኪኒን ፣ እንደ መርፌ ለበሽተኞች መታዘዙ እንግዳ ነገር አይደለም ። ሕመ ምተኞችን እየተቀበሉ ያለምንም መድ ኃኒት -በጾም ብቻ- የሚያክሙ ድርጅ ቶችና የሚያስተናግዱ የማረፊያ ቦታዎ ችም ጥቂቶች አይደሉም ። በስዊድን ፣ በኖርዌይ ፣ በሜክሲኮ ፣ በጀርመን ፣ በራሺያ ፣ በአሜሪካ ፣ በሕንድ ወዘተ ብዙ ይገኛሉ ። ከዕለት ወደ ዕለት ጥቅ ሙ እየጐላ ከመሄዱ የተነሣ ጾም በመ ደበኛ ሆስፒታሎች ተገቢ ሥፍራውን የሚይዝበት ጊዜ ሩቅ እንዳይደለም ይገመታል ።

መቼም ነገርን ነገር ያነሳዋልና የቤት እንስሳት ማለትም ፡- ላም ፣ በግ ወዘተ ያረባሉ? ልብ-ብለው አይተው እንደሆን ቢሏቸው ቢያረጓቸው ሳር የማይነጩ በት ፣ ውሃ የማይጐነጩበት ጊዜ አለ ። ውሻና ድመትም እንዲሁ ሥጋም ሆነ ወተት ቢያቀርቡላቸው ንክች የማያረ ጉበት ጊዜ አለ ። ለምን እንደሆነ ያው ቃሉ ? ባጠቃላይ የቤት እንስሳትም ሆኑ ፣ የዱር አራዊት በሚታመሙበት ወቅት ፣ ማናቸውንም የሚበላ ነገር እር ግፍ አድርገው ስለሚተውት በቀላሉ ከበሽታቸው እንደሚድኑ ታውቋል ።

በመሠረቱ ማናቸውንም ምግብ መ ተው ፣ በሌላም አባባል ጾም-በእንስሳት ብቻ ሳይሆን በሰው ልጆች ጤንነት ፣ የአካል አቋምና አእምሮን በማዳበር (ሜንታል ፕሮሴስ) ረገድ ያልታሰበ የመሻሻል ለውጥ የሚያመጣ መድኃ ኒት መሆኑን ጉዳዩን ሥራዩ-ብለው የተ ከታተሉት ባለሙያዎች አረጋግጠዋል፤

ጾም ለበሽታ መድኃኒት ነው ሲባል ፣ በቀጥታ ነው ማለት ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ መሆኑ በቅድሚያ መታወቅ አለበት ። በቀጥታም መድኃኒትን የሚ ተካም አይደለም ። በየዋህነት በዚህ እንዳንታለል ባለሙያዎቹ አበክረው ያስጠነቅቃሉ ።

ባለሙያዎቹ የሚሉት ባጭሩ ፣ "ተፈ ጥሮ ራሱን በራሱ ሳይታክት የሚንከባ ከብ ፣ የሚያክም ሐኪም ነው ። ባጠቃ ላይ የአካላችን ክፍሎች (እኛ ሳናውቅ ፣ ሳይስማንም) የሚያከናውናቸው አያሌ ተግ ባሮች አሏቸው ።

ከተግባሮቹም አንዱ ከባድና አድካ ሚው ምግብ የማዋሐዱ (ዳይጀስቲንግ ፉድ) ጉዳይ ስለሆነ ፣ ጊዜ ሳንወስን የም ንመገብ ከሆነ ሕዋሳቶቻችን እረፍት የ ሚሉበት ሰዓት ሊኖር አይችልም ። በተ ለይም ታመን አልጋ በምንውልበት ጊዜ የተገኘውን ካግበሰበስን ፣ ሕዋሳቶ ቻችን ነፃ በሆነ ኃይል በሽታውን ግብ ግብ ገጥመው እንዳያጠቁት ማድረጋች ንን መገንዘብ አለብን ። ስለዚህ በበሽታ የተጋለጠ ወይም የታመመ አካል ፣ ራሱ ን-በራሱ እንዲረዳ ከማናቸውም ምግብ በመከልከል (በመጾም) ፍጹም እረፍት እንዲያደርግ ዕድል መስጠት አስፈላጊ ነው ፣" በማለት ያስረዳሉ። ወይም በሌ ላ አነጋገር የመተንፈሻ፣ የደም መመላለ ሻና የምግብ መዋሐጃ ሕዋሳት ያለ-የሌ ለ ኃይላቸውን አጠራቅመው በሽታን ለማጥቃት የሚችሉት ሰውነታች ንን ከማናቸውም ምግብ በመከላከል (በመጾም) ከባድ የሆነው የምግብ ማዋ ሐዱ ሥራ እንዲወገድላቸውና ፍጹም ዕረፍት እንዲያደርጉ ነፃነት ሲያገኙ ብቻ ነው ማለት ነው ። ዕረፍቱ የአካል ና የአእምሮን ዕረፍት እንደሚጨምር መዘንጋትም የለበትም ።

የአካላችንን ተፈጥሮ ከአንድ በኤሌ ክትሪክ ኃይል ከሚንቀሳቀስ መሣሪያ ጋር ማነፃፀር ይቻላል ። መቼም መሣሪ ያው የሚፈለግበትን ግልጋሎት በሚ ገባ ለማከናወን የሚችለው የመርፌ እ ራስ ከምታህለው ከትንሺ ብሎን አን ስቶ እስከ ትልቁ ድረስ ያሉት ሁሉ ፣ በ ሚያበረክቱት ድርሻ መሆኑን እናውቃ ለን ። ከመሣርያው ጋር ያለምክንያት የተገጣጠመ ዕቃም ሆነ ሌላ መሣሪያ ሊኖር እንደማይችል አያከራክርም ። በዚህም አንጻር ከራስ ፀጉራችን እስከ እግር ጥፍራችን ያሉ የአካል ክፍሎች ያለ ምክንያት የተፈጠሩ ሳይሆን ፣ አካ ላችን ጤናማና ደስተኛ እንዲሆን ፣ እን ዲንከባከቡት ፣ እንዲጠብቁት ሆን ተብ ለው የተቀነባበሩና እያንዳንዳቸውም የሚያከናውኗቸው የሥራ ድርሻዎች እንዳሏቸው ለመረዳት ይቻላል ። ይል ቁንም የአካላችን ተፈጥሮ የሰው ልጅ ከተጠበበባቸው ዘመናውያን መሣሪያዎ ች ሁሉ በአንድነት ሁነው ሊወዳደሩት በማይቻል አስደናቂ ጥበብ የተቀነባበረ የተዘጋጀ (የተፈጠረ) መሆኑን በምንረ ዳበት ጊዜ ለአድናቆታችን ወሰን አይኖ ረውም ። እዚህ ላይ ነቢዩ ዳዊት ስለ ሰው አካል ተፈጥሮ በመገረም ፣ "ድን ቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃ ለሁ ። ሥራህ ድንቅ ነው ፣ ነፍሴም እጅ ግ ታውቀዋለች ፣ "መዝ. 138 ቁ. 14) ሲል የተናገረውን ሳልጠቅሰው አላል ፍም ።

የዚህ ዓይነቱ ጾም የሚጾመው ከጥሩ ምግብ በመከልከል ብቻ ሳይሆን ፣ ማና ቸውንም የሚበላ ነገር-እርግፍ አርጐ በመተውና ከጥሩ ውሃ በስተቀር ምንም ነገር ባለመጠጣት የሚፈጸም ነው ። ጾሙ ለአጭር ወይም ለረዥሙ ጊዜ የ ሚቆይ ሲሆን ፣ የአጭር ጊዜው ጾም በ አንድ ቀን ፣ በሦስት ፣ በአራት ቀን ሊወ ስን ይቻላል ። የረዥሙ ጊዜ ጾም ግን እስከ 40 ቀን የሚዘልቅ ነው ።

የረዥሙ ጊዜ ጾም ያለ ሐኪም ትእ ዛዝ ፣ ያለ ሐኪም ጥበቃ በምንም ዓይ ነት ቢሆን ሊሞከርም ሊፈጸምም የማይ ቻል መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው ። ብዙ ጣጣ አለበትና ።

ምስክረ መጻሕፍት ።

1. ጾም ፣ ለጤንነት አስፈላጊ የሆ ነው ምርጥ መድኃኒት ። (በዶ ክተር አለን ኰት) 12ኛ እትም (1976 ዓ.ም. እ.ኤ.አ)
2. በጾም እንዴት ጤናማና ደስ ተኛ ለመሆን እንደሚቻል ። (በሳሊም ኪብራን) ሕትመት ፡- 1975 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. (ይቀጥላል)



# የጤና ዓምድ

## የስኳር በሽታ

የስኳር በሽታ ለመላው ዓለም ትልቅ ችግር ነው ። በዚህ በሽታ በግምት 2% የ ሚሆነው የዓለም ሕዝብ ስለሚሰቃይና ስለ ሚሞት የዚህ በሽታ ችግር በጤና ጥበቃ ላይ ታላቅ ሁከትን ፈጥሮበታል ። ከስኳር በሽታ ጋር ከተያያዘው ችግር ሌላ በሽታ ውን ለመቆጣጠርም ሆነ ለመከላከል ያለ ው ችሎታአሁንም በቂ ካልሆነ ደረጃ ላይ ነው ።

### የስኳር በሽታ ምንድነው ?

የስኳር በሽታ በተለያዩ ዓመታት ውስጥ በልዩ ልዩ መንገዶች አሁንም ቢሆን የዚ ህን በሽታ መነሻ ጀርሞች መርምሮ ለማግ ኘት አልተቻለም ። አሁን ባለን የዕውቀት ደረጃ የዚህ በሽታ መነሻ ዕጢ በሚያወጣው ኢንሱሊን በተባለው ኬሚካል ላይ ከባድ ጉዳት ስለሚደርስ ነው ሊባል ይቻላል ይኸ ው ዕጢ ከሆድ ወደ ትንሽ አንጀት መግቢያ ላይ ዱዋድነም (—————) ውስጥ ሌላም የሚሰራው ሥራ አለ ። የግሉኩስን መጠን ይቀንሳል ፤ የግሉኩሱን መጠን በደም ውስጥ ይመሰርታል ፣ በሰውነት ውስጥ ያሉትን ሁኔታዎች ከመለዋወጡም በላይ በደም ቧንቧዎች ቅርጽ ላይ ከጊዜ በኋላ ለውጥን ያመጣል ።

### የስኳር በሽታ ይወረሳልን ?

የስኳር በሽታ በቤተሰብ ውስጥ ይታያል ስለዚህ በትውልድ ውስጥ ያልተስተካከለ ሁኔታ አለ ሊባል ይቻላል ። ነገር ግን የስ ኳር በሽታ ያለው ልጅ ይወለዳል ለማለት አይቻልም ቢሆንም ከእስታስቲክ መረጃ ዎች ላይ ምን ያህል ሰዎች ከአንድ ቤተሰብ ውስጥ እንደተያዙ በምርመራ ሊታወቅ ተችሎአል ። የስኳር በሽታ ያለበት ሰው ልጅ እንዳይወልድ አይመከርም ነገሩን ለማመዛዘን ሁለቱም በበሽታው የተለከፈ ልጅ ለመውለድ ያለው ዝንባሌ 20% ያነሰ ነው ።

በበሽታው የተያዙ ባልና ሚስቶች መጀ መሪያ በሽታው ያመጣው ጠንቅ ምን ያህ ል እንደሆነ መረጃዎችን ካገኙ በኋላ ለራሳ ቸው መወሰን ይችላሉ ። ስለዚህ ሁለቱም ሆነ አንደኛው ብቻ በበሽታው ቢያዙም እንኳ በእርግዝና ጊዜ በቂ ጥንቃቄን ማድ ረግ ይኖርባቸዋል ።

### የስኳር በሽታ ምልክቶች

የስኳር በሽታ ዋናው ምልክቱ የሽንት ብዛት ፣ የውሃ ጥማት ፣ ክብደት መቀነስ ፣ ጥሩ የምግብ ፍላጐትና ከባድ ድካም ይሰ ማል ። በተጨማሪ ምናልባት ብልታቸው አካባቢ ያሳክካቸዋል ። ይቆስላል ፣ እንዲ ሁም ዓይንን ይጋርዳል የወር አበባን ያስታ ጉላል (ለሴቶች) ለግብረ ሥጋ ያላቸው ችሎ ታ በጣም ደካማ ነው (ለወንዶች) ከዚህም ሌላ ላልተወሰነ ጊዜ አእምሮአቸውን ስተ ው ይቆያሉ ቢሆንም በብዙ ሰዎች ላይ በቅ ድሚያ ምንም ምልክት አይሰጥም ።

ስለዚህ በመጀመሪያ ምርመራ ከበሽተ ኛው ሽንት ብዙ ግሉኩስ(—————) ስለሚወጣ በሽተኛው በበሽታው ሊጠራ ጠር ይችላል ። ይኸ ጥርጣሬም በደም ውስ ጥ ባለው የግሉኩስ ብዛት (ከፍታ) ሊረጋ ገጥ ይቻላል ። ይኸም ሲደረግ የሚጀምረው ምግብ ሳይበላ ወይም ከትክክለኛው ደረጃ ምን ያህል ከፍ እንዳለ ሲታወቅ ነው በወ ጣቶች ላይ ይህ በሽታ ሳይታሰብ የሚያዛ ቸው ሲሆን ከተቀዳሚ ምልክቶቹ ጋር የተ ያያዘ ነው ። (ይቀጥላል)

የዓለም ጤና ድርጅት መጽሔት
ግንቦት 1979 (እ.ኤ.አ.)

ንብረት አበበ

# ... በተቀደሱ ቦታዎች

ከገጽ ፮ የዞረ

ሙ እንዳዘዙትና በፊርማቸውም አትመው እን ዳጸኑት ደግመው አሳሰቧቸው በ1065 ዓመተ ሒጅራ ዘያ አል ታኢደ በተባለው ወር 17 ቀን ተጻፈ ይህ ትእዛዝ ለእምቢክ ክብር ይግባውና ከይትርታ ጋር ከተከበሩ ጌታችን ሳላህ የኢየሩ ሳሌም አገረ ገዥ ተነገረ።

ይህም ማስረጃ በ1838 ዓመተ .ም. በእሳት ተቃጥሎ ስለጠፋ ኢትዮጵያውያን ተቸገረው በት የነበረ የጉበኦ መንኰሳት ገን የተጠቀመበ ት ነው አሁንም ይጠቀሙበታል የሚያዳዝን ይ ህ ነው። ስለዚህ በእጥፉ አሁንስ እንዴት ተገ ኘ ብሎ መጠየቅም ታሪኳችሁን ሁሉ ለይቶ ለማ ወቅ ያስችላችኋል። አሁን ይህ ሰነድ የተገኘበ ት እውነተኛ ማስረጃ ከዚህ ተገኘ ያለው ጽ ሑፍ ነው። ስለ ትክክለኛው ገልባጭ ተምዝገ የ150 ገንዘብም ሩብእ አል እወል በተባለው ወ ር በ1371 ዓመተ ሒጅራ በ9፡12=1951 ዓመተ ምሕረት ፈረንጅ ፈርማ የመዝገብ ቤት ሹም ውስሬ አል ባይዲ ደግሞ የዋናው ዳኛ የኢየሩሳ ሌም ቃዲ ሻክ ሐልሚ አል ሙሕተሰብ። ማኅ ተም የሕግ አስተዳደር ፍርድ ቤት። ይህ ትክክ ለኛ ገልባጭ የተጻፈው ከአፍ መዝገብ ቤት 15 1ኛ ገጽ 9 የተገኘ ነው። ለዚሁ የጸገብ የተከፈ ለበት 1 ፓውንድ ነው። ለዚሁም የደረሰኝ ቁጥ ር 494767 ነው የተከፈለበት ቀን 10፡12-1951 ዓመተ ምሕረት። ፈርማ ውስሬ አል ባይዲ ማኅ ተም መሐከማ ሽርኢያ አል ቁድስ የኢየሩሳሌ ም የሕግ አስተዳደር ፍርድ ቤት።

በመዝገብ ቁጥር ሰጅል 188 ገጽ ሰፍሐ 211 ላይ የሚገኘው ይቀጥላል

— ኪዳነ ማርያም



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሀገረ ስብከት

## የመስቀል በዓል በታላቅ መንፈሳዊ ሥርዓት ተከበረ

### አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሚከበሩ ዓበይት በዓላት አንደኛው የመስቀል በዓል ነው

ይህም መንፈሳዊ በዓል ከምንጊዜውም በበለጠ መስከረም 16 ቀን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በተገኙበት ተከብሮአል ።

በዚህ ታሪካዊ የመስቀል ዋዜማ በዓል ብፁዓን ጳጳሳት የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች የመንፈሳውያን ወጣቶች ማኅበራትና ምእመናን ተገኝተው "መስቀል መመኪያችን መስቀል ኃይላችን" በማለት በከፍተኛ መንፈሳዊ ድምቀት አክብረውታል ። መስከረም 17 ቀን 1972 ዓ.ም. በዓሉ በከፍተኛ መንፈሳዊ ስሜት ታስቦ ውሎአል ። በየሀገረ ስብከቱም በዚህ ዓይነት የተከበረ መሆኑን ከየቦታው በተላከልን ሪፖርት ለማወቅ ችለናል ።

### አርባ ምንጭ

በጋሞ ጐፋ ሀገረ ስብከት በጨንቻ አውራጃ የተቋቋመው የካህናት ማሠልጠኛ ት/ቤት ለ3ኛ ጊዜ መንፈሳዊ ኮርስ መስጠቱን አስታወቀ ፣ በተላከው ሪፖርት ለመረዳት እንደተቻለው ኮርሱ ከሐምሌ 5 ቀን 71 እስከ መስከረም 5 ቀን 72 ዓ.ም. ሲሆን በኮርሱ ላይ ተሳታፊ የሆኑት ከ7ቱ ወረዳ የተውጣጡ ወጣቶች ሲሆኑ ፣ ካህናትና የሰበካ ጉባኤ አባላትም እንዳሉበት ታውቆአል ።

የማሠልጠኛው ሊ/መንበር ሊቀ መዘምራን ተስፋዬ ዱጊሶ ከመስከረም 5-8/1972 በተሰጠው ሰሚናር የሰበካ ጉባኤን አቅዋም ለማጠናከር ለመጀመሪያ ጊዜ የሰበካ ጉባኤ አስተዳደር በአውራጃ ደረጃ የተቋቋመና አባላትም የተመረጡ መሆናቸውን ገልጸው ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ለተመራቂዎቹ የሥራ መመሪያ በመስጠትና ሥራውንም በትጋት እንዲመሩ ቃለ ቡራኬ የሰጡ መሆናቸውን ጨምረው አስረድተዋል ።

# ዜና አብያተ ክርስቲያናት

## መጽሐፍ ቅዱስ ወደኩባ ተላከ

ስተት ገርት

በተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበራት አማካይነት 10ሺ ሙሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ኩባ ተላኩ ግምታቸው 76ሺ የኢትዮጵያ ብር የሆኑት እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ የኩባ መንግሥት ለኩባ ኢኩ ዩሚኒካል ካውንስል ፈቃድ ሰጥቷል ። እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት "እግዚአብሔር ዛሬ ይናገራል" የሚል መለያ ሽፋን ያላቸውና በቀላሉ ለማንበብና ለመረዳት እንዲቻሉ ሆነው በጊዜው የስፓኒሽ ቋንቋ የተዘጋጁ ሲሆን በፕሮቴስታንትና በካቶሊክ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የተተረጐሙ ናቸው ።

የተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበራት ለመጨረሻ ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ኩባ የላኩት በ1977 (እ.ኤ.አ) 2500 የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሲሆን የአሁኑ ከመቼውም ጊዜ በቁጥር የበለጠ እንደሆነ ተገልጿል ።

ኢኩዩሚኒካል ፕሬስ ሰርቪስ
ቁ 23 46ኛ ዓመት 1979 (እ.ኤ.አ)
ነሐሴ 30/79 ዓ.ም.

## የራሺያ ቤተ ክርስቲያን ሴቶችን ለተልእኮ ታሠለጥናለች

ሌኒንግራድ ፦

የራሺያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን በቀሳውስት ማሠልጠኛ ተቅዋምዋ ለመጀመሪያ ጊዜ ሴቶችን ተቀበለች ። ከመስከረም ወር 1972 እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ጀምሮ 25 ሴቶች በሌኒንግራድ አዲስ በተከፈተው የቤተ ክርስቲያን ሙዚቃ ት/ቤት ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ጥናታቸውን ይከታተላሉ ። ከሦስት ዓመታት በኋላ ሴቶቹ የቤተ ክርስቲያን ሙዚቃ መሪጌቶች ይሆናሉ ። "ቤተ ክርስቲያናችን ሴቶችን ለተልእኮ ስትቀበል በታሪካችን ሁሉ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው" አሉ የቮበርግ ሊቀ ጳጳስ ኪሪል ። ሊቀ ጳጳሱ ይህን ያስረዱት በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ለስብሰባ በተገኙበት ዕለት ነበር ።

ለቤተ ክርስቲያን ተልእኮ የሚሠለጥኑ ሴቶች ከ18 እስከ 32 ዕድሜ ያላቸው ናቸው ። ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ፈጽመዋል በኮርሱም ውስጥ ዜማና (ቅዳሴ) ነገረ መለኮት ያጠናሉ ሲል ኢኮዩሚኒካል ፕሬስ ሰርቪስ ገለጠ ቁ. 24 መስከረም 13 1979 (እ.ኤ.አ.)

## በኢንግላንድ የምትገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን ወርኃዊ ጋዜጣ አዘጋጀች

ሎንዶን "ጽዮን ማርያም" በመባል የተሰየመችው በሎንዶን የምትገኝ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን በየወሩ የሚታተም የእንግሊዝኛ ጋዜጣ ማዘጋጀት ጀመረች ። የመጀመሪያው እትም የወጣ ባለፈው ነሐሴ ወር 1971 ዓ.ም. እንደ ኢትዮ. አቆጣጠር ሲሆን በየወሩ ያለማቋረጥ እንደሚታተም ታውቋል የጋዜጣው ይዘት

ሀ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን ታሪክ ባጭሩ

ለ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን የነገረ መለኮት ትምህርት

ሐ/ የአጽዋማትና የበዓላት ቀኖች

መ/ መልእክት ከመጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን ወቅታውያን ዜናዎችንም ይዞአል።



የጋዜጣው ዐርማ

በሎንዶን ያለችው ኢትዮጵያዊት ቤ ክርስቲያን የምትመራው በአርኪ ማንድራይት (ሊቀ ቀሳውስት) አባ አረጋዊ ወልደ ገብርኤል ኤም.ኤ. ነው ። ቤተ ክርስቲያንዋ ከተመሠረተች 6 ዓመታት ሲሆናት ባሁኑ ጊዜ ሁለት መቶ ቀዋሚ ምያን አባሎች ይገኙባታል ። ባለፈው ዓመት ከተሾሙት 13 ጳጳሳት አንዱ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ከሚመሩአቸው አብያተ ክርስቲያናት አንድዋ ይህች በሎንደን የምትገኘው ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክርስቲያን ናት ። ከዚህም የተነሣ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ በየካቲት ወር 1971 ዓ.ም. ወደ ሎንደን ሄደው በጽዮን ማርያም ቤ/ክርስቲያን ለ4 ደቀ መዛሙርት ዲቁና መስጠታቸውን አዲሱ የኢትዮጵያ ኦ.ተ. ቤ ክርስቲያን በሎንደን የእንግሊዝኛ ጋዜጣ ገለጠ ።



በሎንዶን የኢ.ት.ኦ.ተ.ቤ/ክርስቲያን መሪ አባ አረጋዊ ወ/ገብርኤል

## አዲሱ የካንተርበሪ ሊቀ ጳጳስ ተሠየሙ

ሎንደን 57 ዕድሜ ያላቸው የቅዱስ አልበንስ ጳጳስ ሮበርት ራንሲ በሚቀጥ



የካንተርበሪው ሊቀ ጳጳስ ሮበርት ራንሲ

ለው ዓመት 1980 (እ.ኤ.አ) ጡረታ በሚወጡት በሊቀ ጳጳስ ዶክተር ዶናልድ ኮጋን ምትክ አንድ መቶ ሁለተኛ የካንተርበሪ ሊቀ ጳጳስ ሆነው መስከረም 7 ቀን 1979 (እ.ኤ.አ) ተሹመዋል ። ሊቀ ጳጳሱ በብሪታንያና በዓለም ሁሉ ለአሉ 65 ሚልዮን አንግሊካውያን መንፈሳዊ መሪ ይሆናሉ ። ሊቀ ጳጳስ ሮበርት ራንሲ የኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ምሩቅ ናቸው ።

ጳጳስ ራንሲ በ1951 (እ.ኤ.አ) ቅስና ተቀበሉ በ1970 ዓ.ም. የቅዱስ አልበንስ ጳጳስ ሆኑ ። ከ1973 ጀምሮ የአንግሊካንና የኦርቶዶክስ ሃይማኖታዊ ኮሚሽን ሊቀ መንበር ሆነው ሠርተዋል ። ይህ ኮሚሽን በአንግሊካንና በኦርቶዶክስ መካከል አንድነትን ለመፍጠር የተቋቋመ ነው ። በዚህ ምክንያት ሊቀ ጳጳሱ ስለ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጥልቅ ዕውቀትና ፍጹም ፍቅር አላቸው አዲሱ የካንተርበሪ ሊቀ ጳጳስ የሴቶችን ቅስና ይቃወማሉ ። በዚህም ራሳቸውን እንደ ፍጹም ካቶሊክ አድርገው ይቆጥራሉ ። የሊቀ ጳጳሱን ሹመት ያጸደቁትና ያወጁት ንግሥት ዳግማዊት ኤልሳቤጥ መሆናቸውን በአዲስ አበባ የሚገኘው የእንግሊዝ ቤ/ክርስቲያን ቄስ ኮሊን ባትል ገለጡ ።

# ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ሥራች ሥነ ጽሑፍ ድርጅትና በኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር መሆኑን ልንጠቁምዎ እንወዳለን ።

***

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ተንበርክኮ መጸለይ ይፈቀዳል ወይስ አይፈቀደም? ሁለተኛ፦መጽሐፍ ቅዱስ በትግርኛ ቋንቋ ተተርጉሞ ለሰፊው ሕዝብ ተዳርሷል ግን አንዳንድ ግለሰቦች የፕሮቴስታንት እንጂ የእኛ አይደለም ይላሉ ልክ ናቸው ?

በክርስቶስ ወንድማችሁ
ተስፋ ወልዳይ
ከማኅበረ መንእሰይ ፍኖተ ብርሃን
አሥመራ

አቶ ተስፋ ወልዳይ ከሁሉ በፊት የጌታችን ጸጋ ይብዛልዎ ተንበርክኮ መጸለይ በቤተ ክርስቲያናችን የተፈቀደ ነው ። ሦስት የስግደት ዓይነቶች አሉ ለምሳሌ አድንና አንገትን በማዘንበል አስተብርኮ በጉልበት ተንበርክኮ ሰጊድ በግንባር ወድቆ መጸለይ እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል ነዌና 6፥ 12-13 ። ኤፌ 3፥ 14-19

በትግርኛ ቋንቋ የተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስ የፕሮቴስታንት ብቻ አይደለም እኛም እንቀበለዋለን እንደዚህ የሚሉትን ሳይሰሙ ቅዱስ መጽሐፍዎን ያንብቡ





www.ethiopianorthodox.org

# ሊቃውንቶቻችን

## ስመ ጥሩውና ታላቁ ሊቅ መምህር አካለ ወልድ ሠርፀ ወልድ

ባለፈው ጊዜ ስለኢትዮጵያ ሊቃውንት የትምህርት ይዘትና የታሪክ ሒደት በአጠቃላይ በጽሑፍ በገለጽንበት ጊዜ የሊቁ የመምህር አካለ ወልድ ፎቶግራፍ በመጽሔቱ ላይ ሲታተም ዝርዝር ታሪካቸው ያልተተነተነ በመሆኑ እነሆ አሁን ከዚህ ተጥሎ ተገልጿል።

መምህር አካለ ወልድ ከመንዘው ከመምህር ሠርፀ ወልድና ከመርሐ ቤቴዋ ከወይዘር ወለተ ኪርስ "ገድመፋራ ውቢት" በምትባል አምባ በ1824 ዓ.ም. ተወለዱ።



ስመ ጥሩ ሊቀ መ/አካለ ወልድ ሠርፀ ወልድ

### ትምህርት

ሊቁ ከስድስት እስከ አሥራሁለት ዓመት በነበረው ዕድሜያቸው በእናትና አባታቸው ቤት ሆነው የመጀመሪያውን የትምህርት ደረጃ ተከታተሉ።

ተጥሎም በየድላ በዳባት ማርያም "አባ ጫልቱ" ከተባሉ መምህር ቅኔ ከነአገባቡ ከተማሩ በኋላ የቅኔ መምህር ሆነዋል።

ከዚያም ወደጉንደር ሔደው በዮሐንስ ወልደ ነጉድጓድ ደብር ባንድ በኩል ቅኔ እያስተማሩ በሌላ በኩል ደግሞ በበዓታ የብሉያትን ትርጓሜ በሚገባ አድርገው አጠኑ።

ገና ከሕፃንነት ዕድሜ ጀምሮ መማር ማስተማር ትዕግሥትና ችሮታ በአንድነት ተጣምረው በመምህር አካለ ወልድ ሕይወት ላይ በማንፀባረቃቸው በእነዚህ ዓይነቶቹ ተግባራውያን ይዘቶቻቸው የሚያውቃቸው ሁሉ ይደነቅ እንደነበረ በጉልህ ይነገራል።

በኋላም በአጣጣሚ ሚካኤልና በእልፍኝ ጊዮርጊስ የሐዲሳትንና የመጻሕፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ ተማሩ። በተከታታይም የመጻሕፍተ መነኮሳትን ትርጓሜ ከመምህር ሀብቱ አጥንተው የአራቱ ጉባኤያት ሊቅ ሆነዋል።

ሊቁ ማናቸውንም ዓይነት የትምህርት ምርምርና የሃይማኖት ምሥጢር ሲጠየቁ ያለአንዳች ችግርና ማመንታት ሊያስረዱ የሚችሉ በብልህነት በዕውቀትና በትዕግሥት የተዋቡ ፤ የልታወቅባይነትና የሹመት ፍትወት የጠፋላቸው ፍጹም ሰው ስለነበሩ ሁኔታቸውን በቅርብ የተረዱት ብዙዎች ሊቃውንት በትዕግሥታቸው ከኢዮብ በቸርነታቸውና በፍጹም ሃይማኖታዊነታቸው ከአብርሃም በሊቅነታቸው ከነመምህር ኤስድሮስና ከነአራት ዓይና ጉሹ ያወዳድሯቸው ነበር።

ከዚህም የተነሣ ዓፄ ቴዎድሮስ በጣም ስለአወቋቸው ሊረዱ የሚፈልጉትን ሁሉ ሲጠይቋቸው በሚሰጡዋቸው አጥጋቢ መልስ እየተደሰቱ ከሌሎቹ ሊቃውንት ሁሉ በበለጠ ይንከባከቡዋቸውና በአክብሮት ይመለከቱዋቸው ነበር።

### "ይማሩዋል እንደአካል ይዋጉዋል እንደገብርዮ"

ይህ የፍሬያማ ሙያ መግለጫ ጥቅስ የተጠቀሰው በዓፄ ቴዎድሮስ ሲሆን በትክክል ሊያንፀባርቅም የቻለው በመምህር አካለወልድና በንጉሡ በዓፄ ቴዎድሮስ የጦር አዝማች በነበረው በጀግናው በፊታውራሪ ገብርዬ ሰውነት ላይ ነበር።

ይኸውም ዓፄ ቴዎድሮስ "ይማሩዋል እንደአካልዬ" በማለት የመምህር አካለ ወልድን ከፍተኛ የትምህርት አቋም ሲገልጡ"ዋጉዋል እንደገብርዬ" ብለው ደግሞ የጦር አዝማቻቸውን የፊታውራሪ ገብርዬን ጀግንነት በይፋ ማረጋገጣቸው መሆኑን ልንገነዘበው ይገባል።

ሊቁ አካለ ወልድም በበኩላቸው የዓፄ ቴዎድሮስን ቆራጥነትና ጀግንነት የሚገልጹ ልዩ ልዩ የሆኑ ቅኔዎች በየጊዜው አበርክተዋል።

በኋላም ሊቁ ወደሸዋ ወደ ዓፄ ምኒልክ በዚያን ጊዜ ንጉሥ ምኒልክ ዘንድ ስለመጡ የቁም ነገርና የትምህርት ሰውነታቸውን ገጽታ ቅደም ብለው በዝና የተመለከቱት ንጉሥ ምኒልክ እጅግ በጋለ ደስታ ተቀብለው ለጉባኤ እንዲያመቻቸው በማሰብ የቁንዲ ጊዮርጊስ ደብር በኋላም የፍርኩታ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አስተዳዳሪነት ሰጥተዋቸ

ወደ ገጽ ፲፭ ዞሯል



# ክርስቲያናዊ ሕይወት

## መተጫጨት በክርስትና ሕይወት

"እግዊ ለልግዱ የሐገር ገመድ የበትሉ ክበድ አለኝ ይላል" የሚል የአበው አነጋገር አለ አባባሉ የሚያመለክተው የጥንት ሰዎች በሚተጫጩበት ጊዜ የሊላቸውን አለን ማለት ያልሆኑትን መስሎ መታየት የተለመደ እንደነበር ነው።

በአሁኑም ጊዜ ቢሆን በሚተጫጩበት ወቅት ግልጥ ባልሆነ መንገድ ይነጋገሩና ከጊዜ በኋላ ጉዳዩ ሲገለጥ ችግር ይፈጥራል። አንዳንዱ ወጣት የሌለውን አለኝ በማለትና ያልሆነውን መስሎ በመታየት የኑሮ ጓደኛ ሊያደርጋት የፈለጋትን ወጣት ያባብላል ። ሌላው ደግሞ ያለውን ቀንሶ ብዙውን አሳንሶ ይናገራል፣ ምናልባት ያልሆነችን እንደሆነ በማለት የግል ገንዘብ ለማስቀመጥ እያሰበ ይሆናል።

ይህ አይነቱ ማባበል በሴት ወጣቶች በኩልም ይታያል፣ ልጃገረድ ሳትሆን "ልጃገረድ ነኝ " ዕጮኛ እያላት 'ዕጮኛ የለጥኝም" በማለት፡ የወጣቱን ኪስ ካረቆተች በኋላ ፊቷን አዙራ የምትሄድ አትታጣም ፤ ከዚህም ጋር ወጣቱ የሚፈልጋት የተማረች ፤ ጥሩ ደሞዝ ያላት ጠባየ መልካምና መልከ ቀና ቆንጆ ይህ ቀረሽ የማትባል እንድትሆንለት ይፋልጋል ፤ በነዚህ ነገሮች እርሱም ፍጹም መሆን እንዳለበት እራሱን ማስተካከል ይኖርበታል እርሱ ከወጣትዋ የሚፈልገውን ሁሉ ወጣቷም ከእርሱ እንደምትፈልግ አያጠያይቅም።

በክርስትና ትምህርት መሠረት ለጋብቻ መተጫጨት በቀላሉ የሚታይ አይደለም ፤ በተፈለገ ጊዜ ዘው ብሎ ገብቶ ሳያስፈልግና አልመች ሲል "ያውልህ ያውልሽ " ተብሎ የሚተው አይደለም የወንዱን ጉድለት ሴቲቱ የሴቲቱን ጉድለት ወንዱ በመታገስና በትምህርት በማስተካከል ችግሩንና ደስታውን በአንድነት እየተከፋፈሉ የሚኖሩበት የአንድነት ዓላማ ነው ይህን በመገንዘብ ጋብቻንና ጓደኛውን ማጥናት ብልህነት ነው ፤ በመተጫጨት ጊዜ መልኩ ደስ አለኝ መልክዋ አስደነገጠኝ በማለት ብቻ ሳይሆን በዕድሜ በትምህርት ደረጃና በመሳሰለው ሁሉ መጠናናት አስፈላጊ ነው፣ ጥናቱ በሚከናወንበት ጊዜ እሱ ለእርስዋ፣ እርስዋም ለእርሱ ግልጥ መሆን ይገባል፣ ወጣቱ ለእጮኛው ጠባዩን ፍላጐቱንና አላማውን ሁሉ ገልጦ ማስጠናትና የኑሮ ጓደኛውም እንዴት ያለች መሆን እንዳለባት ማስረዳት፣ እርስዋም በበኩልዋ አላማዋንና ፍላጐትዋን ገልጣ ፤ ልታገባው የምትፈልገው ወንድ በሕይወቱ እንዴት ሆኖ ቢኖር እንደምትደሰትበት ብታስጠናው ከጋብቻ በኋላ ችግር ላይገጥማቸው ይችላል።

ወጣቶችም ሆኑ ልጃገረዶች የኑሮ ጓደኞቻቸውን ሲመርጡ በጥበብ በብልሃትና በጸሎት ካላደረጉ ፍጻሜው ሊያምር አይችልም አካባቢን ማለት በዕድሜ መመጣጠን፣ ታማኝነትን ጠንቅቆ ማጥናት ያሻል።

የኑሮ ጓደኛን ለመምረጥ የሚረዱ ዘዴዎች 1ኛ ምርጫው ከመወሰኑ በፊት ወላጆች ቢያውቁና ቢመክሩበት ውጤቱ ያምራል፣ 2ኛ የኑሮ ጓደኛን ለመምረጥ ወላጆች ለወጣቶች ዕድል መስጠትና የወጣቶቹንም ምርጫ ትክክለኛነት መመርመር ይገባል። 3ኛ ከጋብቻ አስቀድሞ በመተጫጨት ላይ ሳሉ በፈቃደ ሥጋ አለመተዋወቅ ነው መተጫጨት ጋብቻ ሊጸናና አስደሳች ሊሆን የሚችለው በፍልስፍና ሕግ ሳይሆን አንዱ ለሌላው ራሱን መሥዋዕት በሚያደርግበት በፍቅር ሕግ ነው።

ፍቅርም ሰውን ወደ እግዚአብሔር ስለሚያቀርብ በእምነትና በፍቅር በሚተጫጩ ወጣቶች ላይየእግዚአብሔር መንፈስ ያድራል በእግዚአብሔር ፍቃድ የሚደረግ ነገር ሁሉ የተቃና ይሆናል መተጫጨት ለጊዜያዊ ጥቅምና ፍላጐት ሳይሆን ዘለቄታ ላለው ፍቅር መሆን አለበት ፍቅር ማለትም ይቅርታ፣ መቻቻልና ትዕግሥት ነው፣ ፍቅር ትራራለች፣ ትታገሳለች ሁሉን ታምናለች፣ ፍቅር የቤትን ሁከት ታስወግዳለች የኢኮኖሚን /የገንዘብን/ ችግር ታርቃለች ፍቅር ዕውነተኛ መሥዋዕት ናት፣ ፍቅር የጓደኛን በሽታውን፣ ድኅነቱን፣ሥቃዩን አትጸየፍም ሁሉንም በደስታ ትቀበላለች፣ በፍቅር መተጫጨት በማይለይ አንድነት ተያይዞ እየተረዳዱ ለመኖር እንጂ አንዱ ሌላውን ለመግዛት አይደለም።

መፋቀርና መተጫጨት ለጋራ ጉዳይ መሥዋዕት መሆን ማለት ነው። ፍጹም የሆነች መልካም ሴት ዕጮኛዋን ፍጹምና መልካም ተወዳጅም ልታደርገው ትችላለች፣ ሐሳቡንና ሥራውን ሁሉ እየተካፈለች ብትረዳው ሁሉን ነገር በማሻሻል ርምጃው ይቃናል። ጋብቻን የደስታ ምንጭ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ሴት ባለቤትዋን በሁሉ ብትረዳውና በቤት ለሚከናወነው ጉዳይ ሁሉ መሥዋዕት ስትሆን ነው። ሁለተኛው ደግሞ በትምህርት በደረጃ፣ በአላማና በጠባይ ሲመሳሰሉ ነው። አዋቂው ከአላዋቂው አማኙ ከኢአማኙ ወጣቱ ከአረጀውስምምነት አይኖርምና "ልባም ሴትን ማን ሊያገኛት ይችላል? ዋጋዋ ከቀይ ዕንቁ እጅግ ይበልጣል፣ የባልዋ ልብ ይታመንባታል" ምሳሌ 31. 10 አዎ በፍቅር በእምነትና በጸሎት እግዚአብሔርን የለመነ ያገኛል፣ ስለዚህም ጠቢቡ ሰለሞን በምሳሌው "ቤትና ባለጠግነት ከአባቶች ዘንድ ይወረሳሉ አስተዋይ ሚስት ግህን ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ናት" ይላል 19:14 እንግዲህ መልካምና አስተዋይ ሚስትን፣ እንዲሁም ብልህና አስተዋይ ባልን ለማግኘት የእግዚአብሔር ፈቃድ መኖር አለበት፣ የእግዚአብሔርም ፈቃድ እንዲሆን የእምነት ጸሎት ያስፈጋልጋል።

ራደ አሰረስ



www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

## ማኅበረ ሐዋርያትና ሥራው

ማኅበረ ሐዋርያት በኤርትራ ክፍለ ሀገር በአሥመራ ከተማ የሚገኝ ታላቅ መንፈሳዊ ድርጅት ነው።

ይህ መንፈሳዊ ድርጅት ከተቋቋመ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ለቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ አገልግሎት አበርክቷል።

በመጀመሪያም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ደሙን አፍስሶ ቤተ ክርስቲያንን ሲመሠርታት በ12 ሐዋርያት በ72 አርድእት በ36 ቅዱሳት አንስት በጠቅላላ በ120 ቤተሰብ እንደነበር በሐዋርያት ሥራ በም. 1 ቁ. 5 ተገልጿል።

ከዚያ በኋላ ግን በክርስቶስ ያመኑ ክርስቲያኖች ሁሉ መንፈሳዊ ማኅበርን እያቋቋሙ ቁጥራቸው ከእለት ወደ እለት እየበዛ ይሄድ እንደነበርና ማኅበረ እስጢፋኖስም በሚል ስያሜ የሚጠሩ 8000 ክርስቲያኖች እንደነበሩም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዓምድ ተጽፎ እናገኛለን።

ማኅበረ ሐዋርያትም ያንን የማኅበረ እስጢፋኖስ አሠረ ሃይማኖት በመመልከትና ሥራቸውንም በመከተል ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ባለችበት ጸንታ እንድትኖር የወንጌልም ትምህርት በየአውራጃውና በየወረዳው እንዲሰራጭ ከዚያም አልፎ የወንጌል ትምህርት ላልደረሳቸው ለማዳረስ "ማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት" በሚል ስም የሚጠራ መንፈሳዊ ማኅበር አቋቁሞ በልዩ ልዩ መንገድ ክርስቲያናዊ ተግባርን ሲያከናውን ቆይቷል አሁንም በዚሁ ሥራ ይገኛል።

ስለዚህ ይህ ማኅበር በመጀመሪያ ጊዜ ለምን በምን እንደተቋቋመና ከተቋቋመም በኋላ ምን ዓይነት ክርስቲያናዊ ሥራ እንደ ሠራ ለማብራራት ከማኅበረ ሐዋርያት ዓባሎች 1ኛ መ ሰላም ገብረ መድኅን ተስፋ ሚካኤል 2ኛ ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስን 3ኛ ርእስ ደብር ማኅደረ ተስፋ ሚካኤልን አነጋግረናል።

ትንሣኤ ይህ ማኅበር መቼ ለምን በምን ተቋቋመ?

መልአከ ሰላም ገ/መድኅን ይህ ማኅበር በ1943 ዓ.ም. ተቋቋመ። ዓላማውም በሃይማኖት ያሉ በዚያው ጸንተው እንዲኖሩና ያላመኑትን ለማሳመን ነው ይኸውም ሌሎች እንጋት አብያተ ክርስቲያናት የተለያዩ ድርጅቶችን በማቋቋም ቤተ ክርስቲያናቸውን አስፋፍተው ራሳቸውን ችለው ሌሎችን ሲረዱ እየተመለከትን እኛ ኦርቶዶክሳዊውያን እንዴት እኛችንን አማምረን እንመለከታለን በሚል መንፈ ሳዊ ቅንአት ተነሣሥተን ይህንን ድርጅት ለማቋቋም ችለናል።

ትንሣኤ ይህንን የማኅበረ ሐዋርያትን ማህበር ስታቋቁሙ በራሳችሁ ሐሳብ ነው ወይስ በመንግሥት ድጋፍ ነው የተቋቋመው እንዴት ተቋቋመ?

ሊቀ መዘምራን ሞገስ ማኅበረ ሐዋርያት ለመጀመሀያ ጊዜ ሲቋቋም የመንግሥት ድጋፍ አልነበረውም ሌሎች ሚሲዮናውያን እንደሚያደርጉት ሁሉ እኛም በራሳችን ሐሳብ የተወሰን ሰዎች አቋቋምነው ይኸውም ሃይማኖታችን እንዳይደከም በማኅበር ተደራጅተን አንድ ግዙፍ አካል ያለውን ማኅበር ብናቋቁም ምን ይቸግረናል ብለን ሐሳብ ለሐሳብ ከተለዋወጥን በኋላ በኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን 120 ሰዎች ስብሰባ አደረግን አንድ መቶ ሃያውም ከካህናትና ከምእመናን የተውጣጡ ናቸው በዚህ ዓይነት ድርጅታችን ተመሠረተ።

ትንሣኤ ማኅበሩ በአሁን ጊዜ ስንት አባሎች ይገኙበታል?

ርእስ ደብር ማኅደረ ማኅበረ ሐዋርያት በርከት ያሉ አባሎች አሉት ይህ ማኅበር ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመው በ12 ሐዋርያት በ72 አርድእት በ36 ቅዱሳት አንስት ማለት በ120 ቤተሰብ ምሳሌ ሲሆን አሁን ብዙ አባሎች አሉት

ትንሣኤ ማኅበረ ሐዋርያት ማተሚያ ቤት እንዳለው ግልጽ ነው ነገር ግን ይህ ማተሚያውን ቤት ያገኘው በራሱ ገንዘብ ገዝቶ ነው ወይስ በሌላ ነው ያገኘው በምን እንደተቋቋመ ቢገልጹልኝ።

መልአከ ሰላም ገ መድኅን ማተሚያ ቤቱን ለማቋቋም የሃይማኖት ተቆረቋሪዎች የምግባረ ሰናይ ተሳታፊዎች የሆኑት መንፈሳዊያን ሰዎች በጥሬ ገንዘብ ሆነ በቀንድ ከብቶች ረድተውናል ከዚህም ሌላ በመንግስት ፈቃድ ሎተሪ አዘጋጅተን ባገኘነው ገንዘብና ከባንክም የተወሰነ ገንዘብ ተበድረን ማተሚያ ቤቱን አቋቁመናል።





በማኅበረ ሐዋሪያት ከተሠሩት አ/ ክርስቲያናት መካከል ሁለቱ



ትንሣኤ ይህ ማተሚያ ቤት ከተቋቋመ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ስንት ቅዱሳት መጻሕፍትን አሳትሞአል? ምን ያህልስ ለአንባቢያን አዳርሶአል?

ሊ/መዘምራን ማተሚያ ቤቱ ከ13 ዓይነት በላይ የተለያዩ መጻሕፍትን አሳትሞአል ከነዚህም ውስጥ ከየዓይነታቸው ከ10000 /ከአሥር ሺ.ህ በላይ ለምእመናን በነጻ አድልዋል ከዚህም ሌላ



ሊ/መ ሞገስ ዕቁበ ጊ.

ልደት፣ጥምቀት፣ ስቅለትና ትንሣኤ በመሳሰሉት ታላላቅ በዓላተ በየዓመቱ መንፈሳዊያን ሥነጽሑፎችን እያዘጋጀና እያተመ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ለሚገኙ ምእመናን ያድላል ይህ ብቻ አይደለም የወንጌል መልእክት በሚገባ በክርስቲያኖች ልብ ተቀርጾ እንዲቀር ይልቁንም ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖትን በቀላሉ ለማስተዋወቅ መንፈሳዊውን ፊልምና እንዲሁም በልባቸው የሚያምኑትን እምነት በበለጠ እንዲከታተሉ በስዕል እያስጠና ሌትና ቀን ለማስተማር ይጥራል።

ትንሣኤ በቤተ ክርስቲያን የመጻሕፍት እጥረት እንዳለ ይነገራል ። ታዲያ ይህ ማተሚያ ቤት ምን ያህል ምእመናንን የሚያረካ ይመስልዎታል?

ርእስ ደብር ማኅደረ ተስፋ ሚካኤል በእውነቱ ይህ ማተሚያ ቤት ብዙውን ችግር እንዳቃለለ እንገምታለን ለምሳሌ ሐዲሳትንና ብሉያትን ቅዳሴን ሰዓታትንና የመሳሰሉ የቤተ ክርስቲያን መገልገያዎች ለመግዛት ምን ያህል ችግር እንደነበር ከሁሉም ሥውር አይደለም አንዱን የብራና የቅዳሴ መጽሐፍ ለመግዛት ባጭሩ ከ200-300 የኢትዮጵያ ብር ያስፈልግ ነበር።

ዛሬ ግን ማ ሐዋርያት የሚያሳትመው መጽሐፈ ቅዳሴ ከ8-10 ብር ይገዛል ።

ትንሣኤ ማኅበረ ሐዋርያት ከማተሚያ ድርጅቱ ሌላ ያቋቋማቸው ሌሎች ድርጅቶች አሉ ወይ?

መልአከ ሰላም ማኅበሩ ያቋቋማቸው ድርጅቶች በከፊል የሚከተሉት ናቸው፦

1ኛ / 7 አብያተ ክርስቲያናት አሳንጸዋል

2ኛ / ትምህርት ቤቶችን በብዛት አሠርተዋል።

በማኅበረ ሐዋርያት የታነጹ አብያተ ክርስቲያናት

1ኛ / ደብረ ገዕዛን መድኃኔ ዓለም አሥመራ
2ኛ / ደብረ ብርሃን ሥላሴ
3ኛ / መካነ ሕይወት መድኃኔ ዓለም
4ኛ / መርሶ አሕግር ቅዱስ ሚካኤል ምጽዋ
5ኛ / ቅድስት ማርያም በነገደ ኩናማ ሀገረ ባዜን
6ኛ / ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን
7ኛ / መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ኩናማ ሀገረ ባዜን ናቸው።

ማኅበረ ሐዋርያት ያሠራቸው ት/ቤቶች

1ኛ / ደብረ ብርሃን ሁለተኛ ደረጃ ት ቤት ሃያ ስምንት ክፍል ያለበት አሥመራ
2ኛ / መርሐ-ሕፃናት ት /ቤት
3ኛ / ቀራንዮ ት ቤት
4ኛ / ደብረ ደናግል ት ቤት
5ኛ / በአካለ ጉዛይ አውራጃ ፈለገ ሰላም ት ቤት
6ኛ / ሰንዓፈ ት ቤት
7ኛ / በሠራየ አውራጃ ናዝሬት ት/ቤት
8ኛ ፍኖተ ሰላም ት ቤት
9ኛ በምፅዋ ከተማ ብርሃን አዜብ ት ቤት ናቸው።

በማኅበረ ሐዋርያት የታተሙ መጻሕፍት

1ኛ / መጽሐፍተ ብሉያት 8 ብሔረ ኦሪት ከኩፋሌ ጋር በግዕዝ
2ኛ ዳዊት በግዕዝ
3ኛ ሐዲሳት በግዕዝና በአማርኛ
4ኛ ፍትሐ ነገሥት በግዕዝ
5ኛ 14 መጻሕፍተ ቅዳሴ በግዕዝ
6ኛ / ሕዝብ የሚገለገልባቸው ልዩ ልዩ የጸሎት መጻሕፍት በግዕዝና በአማርኛ
7ኛ / የጋብቻ ምስክርና ሕፃናት ሲጠመቁ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት
8ኛ / መልክዓ ጉባኤና ሰዓታት የመሳሰሉትን አሳትመዋል

በማኅበረ ሐዋርያት የሚካሄድ ተግባረ እድ

1ኛ / የሥጋጃ ሥራ በወጣቶች የሚካሄድ
2ኛ እርሻ እርሻውም የሚካሄደው በዘመናዊ መሣሪያ ትራክተር ነው

በማኅበረ ሐዋርያት የሚተዳደሩ መምህራን

| | |
|---|---|
| የመጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሚ መምህራን | 2 |
| የድጓ መምህራን | 4 |
| የቅዳሴ | 4 |

የቅኔ መምህር 1 በጠቅላላ 11 መምህራን አሉት።

ከነዚህም ሌላ የወንጌል ሰባክያን ይገኛሉ።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናትና ትምህርት ቤቶችን ሌሎችንም ሥራዎች ሁሉ በደምብ እየተቆጣጠረ ተገቢውን ባጀት መይቦ የሚያካሂደውና የሚያስተዳድረው ማኅበረ ሐዋርያት ነው። ይሁን እንጂ ማኅበረ ሐዋርያትን ለማዳከም ማኅበሩም እንዲበተን ሌት ከቀን የማይተኙ አንዳንድ ግለሰቦች መኖራቸው ሥውር አይደለም ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ልታስብበት ይገባታል

ቤተ ክርስቲያን ራስዋን በራስዋ ለማስቻል ያለባትንም ችግር ለማስወገድ በየክፍላተ ሀገሩ የሰበካ ጉባኤን በየቤተ ክርስቲያኑ በማጠናከር ላይ መሆኑን በጋዜጣ በመጽሔትና በልዩ ልዩ ማሠራጫዎች እንሰማለን።

ታድያ እኮ በየቤተ ክርስቲያኑ የሰበካ ጉባኤ እንዲቋቋም ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ምእመናኑ ዓቅማቸው በሚፈቅድላቸው መጠን አስተዋጽኦ እያደረጉ ቤተ ክርስቲያን የምትሻሻልበትን ዘዴ እንዲፈጥሩ ነው።

ይሁን እንጂ ይህ ጉዳይ ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ መሆኑን ቀደም ብለው የተገነዘቡ የማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት አባሎችም መንፈሳዊ ማኅበርን አቋቁመው የጎጆ እንዱስትሪን እያካሄዱ ክርስቲያናዊውን ሥራ በማስፋፋት እንዳሉ እነሆ ከላይ በዝርዝር የተገለጡ ሥራዎች የዓይን ምስክሮች ናቸው።

ዛሬም ቢሆን በከተማም በገጠርም ባለች ቤ ክርስቲያን የሰበካ ጉባኤ ይደራጅ እየተባለ የሚደከመው ድካም በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ የደብር አለቆች የገዳም አበምኔቶች የማኅበረ ሐዋርያትን ፈለግ ተከትለው ቤተ ክርስቲያንን ራሷን እንዲያስችሏት ለማድረግ ነው።

ከነፈረግብ ግርቆስ

## ሊቃውንቶቻችን

ከገጽ ፲፪ የዞረ

ዋል ።

በዓፄ ዮሐንስና በንጉሥ ሚኒልክ መካከል በጊዜው ተፈጥሮ የነበረውን አለመግባባት ለማስወገድ የሸዋ ሊቃውንት ወደ ትግራይ ክፍገለ ሀገር በሄዱበትም ወቅት ሊቁ አካለ ወልድ የዚህ ከፍተኛ ተግባር ተሳታፊ እንደነበሩ በታሪክ ተረጋግጧል ።

## ሊቁ ያበረከቱት የትምህርትና የስብከት አስተዋፅኦ

በዓፄ ዮሐንስና በንጉሥ ምኒልክ መካከል የነበረው መቃቃር በስምምነት ከተለወጠ በኋላ ታላቁ ሊቅ አካለወልድ በወሎ መንፈሳዊ ትምህርትን አስፋፍተው እንዲያስተምሩ ታላቅ አደራ ተጣለባቸው ።

ወደ ገጽ ፲፰ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የወጣቶች ዓምድ

## ወጣቶች እራሳቸውን በንጽሕና እንዴት መጠበቅ ይችላሉ?

በትምህርት ብዙ ለመገፋት ሲሉ ሳያገቡ ብዙ የሚቆዩ ወጣቶች በሕግ አግብተው በተወሰነው ሥነ ሥርዓት ለመኖር እስኪችሉበት ጊዜ ድረስ እራሳቸውን በንጽሕና ለመጠበቅ ብዙ ትግል ስለሚገጥማቸው በዝሙት ኃጢአት የወደቁና ተሰናክለው የቀሩ ጥቂቶች አይደሉም።

ወጣቶች በዝሙት ለመውደቅ ምክንያት ከሆናቸው ነገሮች አንዱ ከጋብቻ በፊት ራስን በንጽሕና መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን አለማወቃቸው ነው። ለምሳሌ አንድ ወጣት ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸም የሥጋዊ ግንኙነት ኃጢአት መሆኑን ባለመገንዘብ "የሥጋ ፍላጎት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስለሆነ ምን ጊዜም መርካት አለበት" በሚል ፍልስፍና ተመራና 1ኛ በትምህርት ቤት ካሉት ጓደኞቹ መካከል የልጃገረድ ጓደኛ በማበጀት ቀስ በቀስ ወደብልግና ሥራ አምርቶ የብዙዎችን ክብረ ንጽሕና በመድፈር በእጭር እንዲቀጩ አደረገ፤ ከዚህም የተነሳ ብዙዎች ልጃገረዶች የብዙዎች ልጆች እናቶች እየሆኑ ትምህርታቸውን እስከማቋረጥ ደረሱ።

2ኛ በቤት ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩትን የቤት ሰራተኞች በቃላት እየደለለ በውድም ሆነ በግድ በመድፈር ሠርተው እንዳይበሉ መሰናክል ከመሆኑም በላይ አባት የሌለው ልጅ እንዲያሳድጉ በማድረጉ ከፍተኛ በደል ፈጸመ።

3ኛ በሴትኛ አዳሪዎች ቤት እየሄደ የግል ፍላጎቱን ለማርካት ገንዘብ ስለሚያስፈልገው ማታ ማታ ካባቱ ኪስ መስረቅ ጀመረ። ቀጥሎም ከቤት ያለውን ዕቃ እየወሰደ በሽሽግ ከመሸጥ አልፎ ወደ ጎረቤት ተዛምቶ ጭር ሲልለት ቁልፍ እየሠበረ ሬድዮና ቴፕ የመሳሰሉትን ዕቃዎች በመሸጥ የስርቆት ተግባሩን ቀጠለ ። ይልቁንም በጣም የሚያሳዝነው ትምህርት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ 11ኛ ክፍል እስከደረሰበት ጊዜ ድረስ ሁል ጊዜ በፈተና 1ኛ ይወጣ የነበረ ጎበዝ ይህንን መጥፎ ድርጊት ከጀመረ ወዲህ ያለው የትምህርት ችሎታ እንዳልነበረ ሆነና ከፈተና እየወደቀ በ11ኛ ክፍል ብቻ ሁለት ዓመት ደገመ በ3ኛው ግን ከትምህርት ቤት እንዲባረር ሆነ በዚህም ምክንያት ሲያጋጥመው የሰው ኪስ እየበረበረ ፣ ሲያጣም እየቀላወጠ በየመጠጥ ቤቱ የሚዞርና እየሰከረ በየበረንዳው የሚያድር ደንበኛ ዱርዬ ሆነ። ነገር ግን የዚህ ወጣት ፍልስፍናና አስተሳሰብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚስማማ አልነበረም።

ምንም እንኳን "በጌታ ዘንድ ሴት ያለ ወንድ፣ ወንድም ያለሴት" ሊሆን ባይችልም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከጋብቻ ክልል ውጭ ሊፈጸም አይችልም። ስለሆነም በጋብቻ ክልል ውስጥ እስከተገኙ ድረስ እያንዳንዱ ራሱን በንጽሕና በቅድስናና በክብር ሊጠብቅ ይገባዋል ይህንን ቅድስና የሚጥል ቢኖር ግን እግዚአብሔርን የጣለ በመሆኑ በሥጋው ፍርድ ይቀበላል /1ኛ ተሰ. 4፥8 1 ቆር 3፥17/ ስለዚህ "ከዝሙት ሽሹ ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው። ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአት ይሠራል" ይላል ሐዋርያ ቅ. ጳውሎስ /1ቆር. 6፥18

በግልጥም ሆነ በሥውር ከሴትኛ አዳሪዎች ጋር የሚወሰልቱ ወጣቶች ሥጋዊና መንፈሳዊ ጉድለት በራሳቸው ላይ ያመጣሉ እንጂ የሚጠቀሙት ነገር የለም። በሥጋዊ ረገድ ጤንነታቸው በአባለዘር በሽታ ሊታወክ ሲችል በመንፈሳዊ ረገድ ደግሞ በተሠወረ ኃጢአታቸው ከእግዚአብሔር ተለይተው ሰላምና ደስታ ያጣሉ። ይህ ብቻ ሳይሆን ዝሙት እየተለማመዱና በአጉል ጠባይ ተመርዘው በክርስቲያኖች መካከል ሲመላለሱ ለሌሎች ሰዎች መሰናክል በመሆን የእግዚአብሔርን በረከት ሊያስቀሩ ይችላሉ። እያንዳንዱ ወጣት ደግሞ "ከእጮኛ ጋር ሥጋዊ ግንኙነትን ማድረግ ኃጢአት አይደለም " ብለው በማሰብ ያለሥጋት ግብረ ዝሙት ይፈጽማሉ። በክርስትና ሕግና በክርስቲያኖች አስተያየት ግን ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሁሉ ማመንዘር ነው። ለምሳሌ በ1ኛ ቆሮንቶስ 6፥15 ላይ "ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልት እንደሆነ አታውቁም? "ሲል በአጠቃላይ ይናገራል እንጂ ከእጮኛ ወይም ከሴትኛ አዳሪ ጋር አይልም ስለሆነም «ጋለሞታ »የሚለው ቃል አንዳንዶች የሚሰጡት አስተያየት "ሚስትነቷ በቃል ኪዳን ጋብቻ ሳይረጋገጥ ከወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የምትፈጽም ሴት " የሚል ነው ለምን? ቢባል መተጫጨት ወደ ጋብቻ ለማምራት የሚደረግ በቃል ኪዳን የተወሰነ ሕጋዊ ጋብቻ አይደለምና ነው።

በአጠቃላይ የመተጫጨት ዘመን የመተዋወቂያ ወይም የመመዘኛ ጊዜ ነው። የፈተና ወቅትም ሊሆን ይችላል ። እንዲያውም አንዳንድ ወጣቶች ልጃገረዶችን የመቀራረቢያ ዘዴያቸው እገባሻለሁ የሚለው ዘዴ ሲሆን ወደድኩሽ ከእንግዲህ አልከዳሽም ልሰበር ልሰንጠር በማለት የሚደረድሩት መሐላና የመደለያ ቃል ነው ። ይልቁንም በቤታቸው ሚስትና ልጆች ያሏቸው ወንዶች ሳይቀሩ እድራሻቸውንና ስማቸውን እየቀያየሩ በመንገርና ሚስትና ልጆች ያሏቸው መሆኑንም በመደበቅ እገባሻለሁ እያሉ በማታለል ጊዜያዊ ፍቃዳቸውን ለመፈጸም የሚፈልጉ እንዳሉም ይነገራል ። ይህ የድለላ ቃል በወንዶች ብቻ ሳይሆን በሴቶችም የሚታይ ነው።ለምን? ቢባል እናገባሃለን እያሉ እስከ ጊዜው ድረስ በወንዶች ገንዘብ ለመጠቀም የሚፈልጉ በመጨረሻ ግን ምክንያት እየፈጠሩ አይንህን አልየው የሚሉ ልጃገረዶች መሳይ ሴቶች እንደሚይታጡ ለመገንዘብ ይቻላል ታድያ እንደዚህ ዓይነቱ መተጫጨት ሕጋዊ ጋብቻ ነው ሊባል ይችላል ማለት ነው?

በሌላ በኩል ደግሞ ሁለት እጮኛሞች ለብዙ ጊዜ አብረው ኖረው ጋብቻቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ አለመሆኑን ከተረዱ ሠርጋቸው እሑድ ሲሆን ቅዳሜ ሊለያዩ ይችላሉ። ራሳቸውን በንጽሕና ያልጠበቁ ከሆኑም በዝሙት መውደቃቸው ራሱ ለስምምነታቸው መፍረስ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ወጣት የሚፈልገውን ካገኘ በኋላ «ከኔ ጋር እንዳደረገችው ከሌላም ወንድ ጋር ታደርግ ይሆናል" በሚል ጥርጣሬ ልጅቷን ሊተዋት ይችላል። እንዲያውም ብዙ ወንዶች እጮኛዎቻቸውን እያስረገዙ ስለሚተዋቸው ብዙ ልጃገረዶች ሕይወታቸውን በገዛ እጃቸው እንዳጠፉ ይነገራል። በዚሁ ምክንያት ለትዳር ሳይበቁ አመንዝራ ሆነው የቀሩትንም ቤት ይቁጠራቸው ብሎ ማለፍ የተሻለ ነው። ስለዚህ ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ሥጋዊ ግንኙነት ዝሙት ስለሆነ እያንዳንዱ ወጣት እስከ ጋብቻው ዕለት ድረስ ራሱን በንጽሕና መጠበቅ አለበት እንላለን። ይቀጥላል፡

ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ



# ጥረታችን ለማትረፍ እንጂ ለማጉደል አይደለም

በትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 22 "የቤተ ክርስቲያን ቅርሶችዋ ሰራስዋ ጥቅም ይዋሉ" በሚል ርእስ ታትሞ የወጣውን በማስመልከት "የነበረው እንዳልነበረ እንዳይሆን" በሚል ርእስ ከአቶ ሙሉጌታ ኃይለ ሥላሴ የተሰጠውን አስተያየት በዚሁ መጽሔት ቁጥር 25 ታትሞ ተመልክቸዋለሁ።

በተቀዳሚ አቶ ሙሉጌታን ላመሰግን እወዳለሁ ምክንያቱም 1ኛ መጽሔቱን ተከታትለው አስተያየትዎን በመለገስዎ ሲሆን 2ኛው የሐሳቤ ደጋፊ እንጂ ነቃፊ ሆነው አላገኘሁትምና ነው፤ በአቀረብሁት አስተያየትም ሊተችና አስተያየት ሊሰጥበት የሚገባ ከሆነ ትችቱንና አስተያየቱን አልቀበልም አልልም ።

ትችቱ ግን በቀረበው አስተያየት መሆን አለበት ፣ አቶ ሙሉጌታ ባቀረቡት ሂስ "ተፈላጊ ነገሮች ከቆላም ሆነ ከደጋ ተሰብስበው በዚያው በአዲስ አበባ እንዲቀርብላቸው ፈላጊ ይመስላሉ" ብለዋል እኔ ያቀረብሁትን ጽሑፍ ከማንበብ አልፈው እንደገና በጽሑፍ ገልብጠው ለአንባቢያን ሲያቀርቡ ሀሳቡን የተረዱት አይመስልም፤ ምክንያቱም እኔ ያልሁት በየስብከተ ሀገሩ ለጉብኝዎች አመች በሆነ ቦታ ይደራጁ አልሁ እንጂ ወደ አዲስ አበባ ይሰብሰቡ የሚል ሀሳብ አልሰነዘርሁም፤ ምን አልባት" የሊቀ ጳጳሱ መንበር በሆነው ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ለንዋየ ቅድሳቱ ማደራጃ ቤት መሥራት" የሚለውን ተመልክተው እንደሆነ በየስብከተ ሀገሩና ከዚያም አልፎ በአንዳንድ አውራጃዎች መንበረ ጳጳስና መኖሩን ይረዱ።

አቶ ሙሉጌታ እንዲረዱልኝ የምፈልገው የአንዱ ሀገረ ስብከት ወደ ሌላው ሀገረ ስብከት ሳይዛወር በየስብከተ ሀገሩ ጽሕፈት ቤትና በሊቀ ጳጳሱ አማካይነት ለአጠባበቅና ለጉብኝት አመች በሆነ ቦታ ይደራጁ ማለቴን እንጂ አዲስ አበባ ይሰብሰቡ አለማለቴን ነው።

በእስራ አራቱም አህጉረ ስብከቶች መልክ ባለው ሁኔታ ቅርሶቻችን ቢደራጁ የቱሪስቶችን ጉዞ ያሳጥራል ቱሪስት አስተናጋጁ ሆቴሎችን ያከስራል የገቢ ምንጭን ይቀንሳል የሚሉ ከሆነ ተመልካች ይፍረደው፤ በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ የመጻሕፍትና የቅርጻ ቅርጽ ቅርሶች ይገኛሉ ታድያ ብዙ ያለውም ጥቂት ያለውም ከእሳትና ከፍሳሽ ከሌላም አደጋ የሚከላከል ቤት ሠርቶ ቅርሶቹን መጠበቅና ከትውልድ ወደ ትሥውልድ ማስተላለፍ ይቻላል ማለት ዘበት ነው። በክፍለ ሀገር በአውራጃ፤ በወረዳ እየተጠና በአንድ ላይ ቢደራጁ ግን የተሻለ እንደሚሆን ይገመታል። እስከ አሁንም ይህ ባለመደረጉ የጠፉብንና የተበላሹብን ቅርሳቅርስ ጥቂቶች አይደሉም። ለምሳሌ ያህል በአንድ ቤተ ክርስቲያን ከተመለከትናቸው ና ጉዳት ከደረሰባቸው መጻሕፍት የአንዱን ፎቶ ከዚህ በታች እንመልከት።



በአይጥና በሌት ዎፍ የተቈነጻጸለው የዜማ መጽሐፍ

ይህ በአይጥና በሌሊት ወፍ ተቆነጻጽሎ የምናየው መጽሐፍ በመቶ የሚቆጠር ዕድሜ ያለው ነው። ታድያ እንደሚታየው ሁሉ ከብራናውና ከቀለሙ አንዳችም የዕርጅና መልክ ሳይኖርበት ከአይጥና ከሊሊት ወፍ መከላከያ በሌለው ዋሻ ተሸጉጦ ስለኖረ ከመሰል ቅርሶችና ንዋየ ቅድሳት ጋር እንዲህ ያለ ጉዳት ሊደርስ ችሏል፤ አንዱን ለምሳሌ አቀረብን እንጂ በርከት ያሉ መጻሕፍት ከዚህ በባሰ ሁኔታ ተጐድተዋል። ይህን የተመለከትነው በአንድ ቤተ ክርስቲያን ነው። ከየአብያተ ክርስቲያናቱ ተዘዋውረን ብንመለከት ከዚህ የበለጠ ጉዳት ደርሶ እንደሚገኝ አይጠረጠርም።

ታዲያ እንደ አቶ ሙሉጌታ አስተያየት ቅርሶቻችን በየአካባቢያቸው በአንድ ላይ ቢደራጁና ቢጠበቁ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል ከተባለ ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው መጻሕፍቱ በአይጥ ተበልተው በሌሊት ወፍ ተቊነጻጽለውና በፍሳሽ እርሰው ቅርጻቅርጹም በአፈር ተበልተውና በዝገት ተበላሽተው ይቅሩ ከማለት በቀር ሌላ ትርጉም አይኖረውም።

የእኔም ሆነ የአቶ ሙሉጌታ አስተያየት የቅርሶቹ ህልውና የሚጠበቅበትን መንገድ ለማመልከት ስለሆነ፤ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥር የተቋቋመው የመጻሕፍት፣ የንዋየ ቅድሳትና ቅርሳቅርስ መምሪያ ቢያስብበትና በተገቢው መንገድ ቢሠራ ቅርሶቻችን ከጉዳት እንደሚድኑ አይጠረጠርም ።

ራደ አስረስ



www.ethiopianorthodox.org

# ሐዋርያት ለተረሱ ሕዝቦች

ባለፈው ጽሑፍ ቤተክርስቲያን ወደ ተረሱ ሕዝቦች ሐዋርያትን ልካለችን? የተላኩትስ ሐዋርያት ተልኮአቸውን ፈጽመዋልን? ለሚለው ጥያቄ ታሪክን በመመርኮዝ ትምህርታዊ ማብራሪያ እንደሰጠን ይታወሳል ። አሁን ደግሞ ወንጌልን በኢትዮጵያ ለተረሱ ሕዝቦች እናስተምራለን በማለት ከተለያዩ አገሮች አዳዲስ ሐዋርያት ወደ ኢትዮጵያ ገብተው የሰጡትን አገልግሎት እናቀርባለን።

የኬልቄዶን ጉባኤ በ451 ዓ.ም ከተከናወነ በኋላ ወንጌልን ለማስተማር የክርስትና እምነትን ለማስፋፋት የተረሱ ሕዝቦችንም የክርስቶስ ቤተሰብ ለማድረግ ዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ በገቡ ጊዜ ምን ችግር እንደገጠማቸውና የሰጡት አገልግሎት ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ እንመራመራለን።

ለምሳሌ ሐዋርያት በልዩ ልዩ ክፍለ ዓለም እየተዘዋወሩ ወንጌልን ለተረሱ ሕዝቦች ሲያስተምሩ እሥራት ፣ ግርፋት ፣ ስቅላት፣ መጉላላት እንደደረሰባቸው የቤተክርስቲያን ታሪክ ይመሰክራል ዘጠኙ ቅዱሳንም ወደ ኢትዮጵያ በገቡበት ጊዜ እንግዳ መቀበል ባህሉ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ መልካም አቀባበል አድርጐላቸዋል። ስለዚህ ከደስታ በቀር አንዳች መከራ አልገጠማቸውም።

የመጡበትም አገር ከሶርያ አካባቢ በመሆኑ የሚያውቁት ቋንቋ ሱርስት ነበር። በዚህ አኳኋን በመጀመሪያ ጊዜ ሥራቸው አድርገው የተነሱት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዘለአለም ቅርስ ሆኖ እንዲኖር ለተረሱ ሕዝቦችም መስበኪያ ማስተማርያ እንዲሆን ብሉያትንና ሐዲሳትን ከሱርስት ቋንቋ ወደ ግእዝ መገልበጥ ነበር።

ይህንን በሚፈጽሙበት ጊዜ ብዙ ችግር ደርሶባቸዋል ። ከችግሮቹም ጥቂቶቹን ብንጠቅስ

1ኛ / እንደ አሁኑ ጊዜ ወረቀትና ቀለም የመጻሀፍት ማሳተሚያ ስላልነበር የፍየልና የበግ ሌጦ መሰብሰብ ነው። 2ኛ / ብራና የመፋቁና ልዩ ልዩ እፅዋትን ሰብስቦ ጥቁርና ቀይ ቀለም ማዘጋጀት ነበር 3ኛ / ምሁራኑን ሰብስቦ የሱርስቱ ቃልና የግእዙ ቃል እንዲገናኝ የመመካከሩ ነገር ነው።

በመጨረሻ ይህንን ሁሉ አሳክተው ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲጽፉ ብዙ ዘመን ወስዶባቸዋል። ይህንንም ሲሰሩ ወንጌልን እያስተማሩና የክርስትና እምነትም ለተረሱ ሕዝቦች እንዲንፀባረቅ እያደረጉ ነው ። የተነሱበትም ዓላማ ወደ ተረሱት ሕዝቦች ዘንድ ሂደን ወንጌልን እናዳርሳለን፣ በጨለማም ውስጥ ለሚገኙት ታላቅን ብርሃን እናሳያለን የሚል ስለነበር ይህንንም በተግባር ገልጸው አሳይተዋል።

የፈጸሙት ቅዱስ ተግባር ይህ ብቻ አይደለም። መንፈሳዊ ሥነ-ሥርዐትንና ገዳማዊ ኑሮን ከማስተማራቸውም ሌላ የተዋሕዶ ቤተክርስትያን ዕድገት እንድታገኝ ፣ወንጌል እንዲስፋፋ፣ ምእመናን እንዲበዙ በተለያዩ ሥፍራዎች እየሄዱ የተረሱ ሕዝቦችን በማስተማር ብዙ ትሩፋትን አበርክተዋል። በተለይ የአቡነ አረጋዊ ገድል አቡነ አረጋዊ ጉንደር ክ ። እስከሚገኘው እስከ ጋይንት አውራጃ ድረስ ተዘዋውረው የተረሱ ሕዝቦችን እንዳስተማሩ ይናገራል።

በጠቅላላው እነዚህ ዘጠኙ ቅዱሳን ባሕሩን ተሻግረው ወደ ተረሱ ሕዝቦች መጥተው ይህን ቅዱስ ተግባር በመፈጸማቸው የሐዋርያነት ሥራቸውን በተግባር አስመስክረዋል ለማለት ይቻላል ። ይህንም በመሥራታቸው በዚያን ዘመን የነበረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አማኝ የማይሞት ሥራ ሰርተው በሞት ላለፉት ዘጠኝ ቅዱሳን በስማቸው መታሰቢያ ሆኖ እንዲኖር በትግራይ ክፍለ ሀገር ልዩ ልዩ ገዳማትን አሰርቶላቸዋል። የጻድቃን መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል ተብሎ ተፅፎአልና።

እነርሱ ከሞቱ በኋላ ተተኪዎችስ ምን ሠሩ? የሚል ጥያቄ ቢቀርብ የአቡነ አረጋዊ ደቀመዝሙር የነበረው ያሬድ የወንጌልን ትምህርት በመዝሙር እያቀነባበረ በየቦታው በማስተማሩ ከኢትዮጵያ አልፎ በመላው ዓለም ታውቋል። ስለዚህ በአሁኑ ዘመን ያለን የወንጌል መምህራን የነሱን ምሳሌነት ተከትለን የተረሱ ሕዝቦችን እናስተምር የወንጌልንም ብርሃን እናብራ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ሂዱና አስተምሩ ተብሏልና።



## ሊቃውንቶቻችን

ከገጽ ፲፭ የዞረ

ትምህርታቸውም ፍሬያማ የሆነ ውጤትን ለማበርከት ስለቻለ በወሎ አውራጃዎችና ወረዳዎች የክርስትና እምነት ከጊዜ ወደጊዜ እያደገና እየተስፋፋ ሂደ ፣ በዚህም ጊዜ ንጉሥ ሚካኤል በፊት መሐመድ እንዲሁም እነይማሙ አባዋጠው የመሳሰሉትም ሁሉ ወደክርስትና መድረክ እየቀረቡ የክርስቶስ ቤተሰቦች ሆኑ ።

ሊቁ አካለ ወልድ ብዙዎችን ወደክርስቶስ መንግሥት በማቅረብ ፣ ጉባዔ ዘርግቶ ሊቃውንትን በትምህርት በመውለድና አብያተ ክርስቲያናትን በማስተካከል ለወሎ ሕዝብ ብዙ የመንፈሳዊ ሥራ አስተዋፅኦ አበርክተዋል ።

ሳሉስት የተባለው ደራሲ "እያንዳንዱ ሰው የራሱ የዕድል ሥዕል ሠዓሊ ነው" እንዳለው ሁሉ ቸርነትን ምርምርንና ሊቅነትን በራሳቸው ሕይወት ላይ እንደ ሥዕል የሣሉት ራሳቸው ሊቁ መምህር አካለ ወልድ ነበሩ ።

### የደረሰባቸው ፈተና

በእግዚአብሔር ስም የእግዚአብሔርን ቃል በሚያስተምሩ መምህራን ላይ በየጊዜው ከባድና አሰቃቂ የሆነ ፈተና መድረሱ በቅዱሳት መጻሕፍት የታወቀ እንደመሆኑ ሊቁ የሃይማኖትን ምሥጢር አጉልተውና አስፋፍተው በማስተማራቸው እንዲሁም ብዙዎችን ወደክርስትና እምነት በመመለሳቸው በክርስቶስ መንግሥት የተመቀኙ የተንኰል ሰዎች ያስተምሩ ዘንድ ወደሐይቅ ለመሄድ ቁልቢ ከሚባል አካባቢ ሲደርሱ ከተቀመጡበት በቅሎ ጐትተው አውርደው እንደደበደቧቸው ፣ ይልቁንም በጐራዴ ሊያርዷቸው ከመካከላቸው አንዱን ሲሰነዝር ጐራዴው ወደአልታሰበበት ቦታ አምርቶ ከተማሪዎቻቸው አንዱን እንደመታውና እጁ ሰላላ እንዳደረገው ይነገራል ።

ይህንኑም ባለቅኔ እሱን ከተከተሉት ከሐዋርያት ደቀመዛሙርቱ እጁ የደረቀች አንድ ሰው አለ ብሎ ተቀኝቷል ።

### በቦሩ ሜዳ የታየ ድንቅ ተአምርና የመምህር አካለወልድ ሹመት

ከእምባቦ ጦርነት በኋላ ዓፄ ዮሐንስ ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለሃይማኖት በወሎ ከቦሩ ሜዳ ሳሉ ለቦሩ ሜዳ ምሥራቃዊ ክፍል በሆነው በዓፄ ዮሐንስ ተራራማ ቤተ መንግሥት ላይ ከፍተኛ ተአምር ተከሠተ

ወደ ገጽ ፳ ዞሯል

# ሥነ ጽሑፍ በኢትዮጵያ

ባለፈው እትም በሀገራችን በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ የተጀመረው በሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሰማንያ ሰባት ዓመተ ዓለም መሆኑ ተገልጿል። ከዚያ በኋላ በየጊዜው የሥነ ጽሑፍ መስፋፋት ሲደረግ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መስፋፋቱን ትቶ በዚያው ባለበት ደረጃ ቆሞ ይቆይ እንደነበር ታሪክ ያስታውሰናል።

ሥነ ጽሑፍ ቋንቋን አምልኮን ድጋፍ አድርጐ በትምህርት ይዘት የሚራመድ በመሆኑ ለቋንቋ ለሃይማኖትና ለትምህርት ቀናተኞች የሆኑ መሪዎች ሲነሱ ሥነ ጽሑፍም ከፍተኛ ዕድገትን ያሳያል ለወገን ለሀገር ለአምልኮ ለቋንቋ ትምህርት በጠቅላላው ለሀገር እድገት የማያስቡ መሪዎች በተነሱበት ወቅት ደግሞ ሥነ ጽሑፍ ሲቆረቆዝ በታሪክ እንመለከታለን።

ከ4500 ዓመተ ዓለም ወዲህ ከሰለሞናን ከንግሥተ አዜብ የተወለደው ቀዳማዊ ምንልክ በ4523 ዓመተ ዓለም መንግሥቱን ከታሪክ እንረዳለን በእርሱ ዘመን ከእሥራ ሁለቱ ነገድ እስራኤል ተወጣጥተው ወደ ሀገራችን ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ የሊቀ ካህናቱ የሳዶቅ ልጅ አዛርያስም ታቦተ ጽዮንንና ከእርሱም አስቀድመው ተጽፈው የነበሩትን ቅዱሳት መጻሕፍትን ይዞ መጥቶ በኢትዮጵያዊያን ሊቃውንት በኢትዮጵያ ቋንቋ እንዲጻፍ ስላደረገ የእግዚአብሔር አምልኮት በሰፊው ታወቀ መጻሕፍቱም በጠቅላላ ከዕብራይስጥ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ቋንቋ እየተተረጐሙ ተጽፈዋል ይህም ዘመን ለሀገራችን የሥነ ጽሑፍ መስፋፋት ከፍተኛ ድርሻን አበርክቷል ለማለት ያስደፍራል።

በሀገራችን የመጀመርያ ጽሑፍ የተመሠረተበት የግዕዝ ቋንቋ መሆኑን አንዳንድ የታሪክ ጸሐፊዎች ቢጠቁሙም በሀገራችን በኢትዮጵያ የነበረው ቋንቋ ግዕዝ ብቻ ነበር ለማለት ያዳግታል ቀደምትነት አላቸው ተብለው ከሚጠቀሱት ም ቋንቋዎች ግዕዝ አረሞ ሻንቅላ የላስታ አገው ደንቢያ ጋፋት ዘላን የዳሞት አገው ቋረኛ ናቸው ይሁን እንጅ ከተጠቀሱት ቋንቋዎች መካከል ፊደል ያለውና ሥነ ጽሑፍ የሚጻፍበት ግዕዝ ሲሆን የቀሩት ግን ፊደሎች ስለሌሏቸው የሚነገሩትና የሚጻፉት የግዕዝን ቋንቋ ጥገኛ በማድረግ ነው።

እንደገና ወደ ታሪክ መለስ ብለን ስንመለከት በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ወደ ሀገራችን የመጣው ምሁር ሊቀ ካህናት አዛርያስ ኦሪቱን ማስተማር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ ከሣቴ ብርሃን አባ ሰላማ ድረስ 1312 ዓመት ይሆናል በእነዚህ ዘመናት ሥነ ጽሑፍ እየተስፋፋና እያደገ ሄዷል።

ከሊቀ ካህናቱ ከአዛርያስ ወዲህ ም ቢሆን የኢትዮጵያ ሰዎች በዓል ለማክበር በዓመት ሦስት ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበርና መጻሕፍቱም በየጊዜው እየተጻፉና እየተስፋፉ ሂደዋል በዳዊትም ጊዜ እስራኤል በፋርስ በባቢሎን ሳሉ ሰንበትን ማክበር ሕገ ኦሪትን አጽዋማተ ኦሪትን በዓላተ ኦሪትን እንደ ጥንቱ ታከብራላችሁን ብለው ለኢትዮጵያውያን ቢልኩላቸው እናንተ በአሕዛብ ሀገር በስደት ወድቃችኋልና ከሕገ ኦሪት በመለየታችሁ እናዝናለን እንጂ እኛስ ከኦሪት ሕግ አልወጣንም ከማንኛውም ሥነ ሥርዓት አልተላለፍንም በማለት ጽፈው ላኩላቸው ተልከው የመጡትም በሚመለሱበት ጊዜ በኢትዮጵያ የሚገኙ በሕገ ኦሪት ያመኑ ሕዝብ እግዚአብሔር የሆኑ ሁሉ ገንዘብ አዋጥተው ዘጠኝ ሊቃውንት የዕብራይስጥ ቋንቋ የሚያውቁ መርጠው ገንዘቡን ሰጥተው ተልከው ከመጡት መልዕክተኞች ጋር በባብ አልመንደብ ተሻግረው የእስራኤል ምርኮኞች ወዳሉበት ሂደዋል ወደ ባቢሎንም በደረሱ ጊዜ ነቢያት ካህናት የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ በደስታ ተቀበሏቸው እነርሱም የተላከላቸውን ገንዘብ አስረከቧቸው በኢትዮጵያ ያሉትም ወገኖቻቸው በሕገ ኦሪት ጸንተው ሲኖሩ እነርሱ በስደት ምክንያት ከሕገ ኦሪት በመለየታቸው እጅግ በጣም አዘኑ።

ከዚያ በኋላ የተላከውን ገንዘብ ሰጥተትው ወገኖቻቸውን ተሰናብተው ሲመለሱ ነቢያት ካህናት ተማርከው ወደ ባቢሎን ከወረዱ በኋላ የተጻፉትንም ቅዱሳት መጻሕፍት ይዘው ወጥተዋል መጻሐፍቱም ሶርያ ዶርብያ ኤቅና አሳኤል ናቸው ከዚያም በኋላ ሥነ ጽሑፍ በግዕዝ ቋንቋ እጅግ በጣም ለመስፋፋት በቅቷል።

የሀገራችን ኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ሁኔታ በተለያዩ አቅጣጫዎች ይነገራል አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች ስለ ሥነ ጽሑፋችን ሲያብራሩ እንደሚከተለው አድርገው ይተነትናሉ የአክሱም መንግሥትና ሕዝብ ከደቡብ ዓረብ ሕዝብ ታሪክ የተጐራበተና የተዛመደ ነው ከፊደሉ ፣ ከሥነ ጽሑፉ ከሥልጣኔውና ከልምዱ ጋር የተያያዘ እንደሆነ እንዲሁም ያን ጊዜ ኢትዮጵያ ወይም የኩሽ አገር ተብሎ የሚጠራው የኑብያ ሕዝብ የስልጣኔ መደብ በናፓታና በመርዌ የነበረው በሃይማኖትም በስልጣኔም በልማድም ከግብፅ ሕዝብ ጋር የተገናኘ መሆኑ እያጠራጥርም ይሉና ወደ ሥነ ጽሑፉ መለስ ብለው በሀገራችን የነበረው ሥነ ጽሑፍ በዮዲትና በግራኝ መሐመድ መነሣትና በሌላው ምክንያት ተደምስሶ እንደገና መዘጋጀት የቻለው ከአሥራ አራተኛው መቶ ዓመት ምህረት ወዲህ ከዓፄ ዓምደ ጽዮን ጊዜ ጀምሮ በመሆኑ ከዚያ ዘመን ወዲህ ከምዕ ጐደል የመንግሥትም የሕዝብም የመንፈሳውያንም ሥነ ጽሑፍ ይገኛል አንዳንድ መንፈሳውያን ጽሑፎች በይኩኖ አምላክ ጊዜ የተዘጋጁ እናገኛለን ከእነርሱም ስምንቱ ብሔረ ኦሪት የሚባሉ መጽሐፍት ናቸው እነርሱም ዛሬ በፈረንሳይ ሀገር በፓሪስ ቤተ መጻሕፍት እንደሚገኙ ይነገራል ።

ከዓፄ ዓምደ ጽዮን ጊዜ በፊት ያለውን የዓስታና ይልቁንም የአክሱምን ታሪክ የቤተ ክህነት ሰዎች መነኮሳትና አጨጌዎች የመንግሥቱም ጸሐፊዎች ሲያያዝ ቃል ሊቃል እየተነገረ የመጣውን ከራሳቸውም አስተያየት ጋር እየጨመሩ ሲጽፉ ለእያንዳንዱ የአክሱምና የላስታ ንጉሥ በዘመኑ የፈጸመውን አሜሜር የጦርነትና የመንፈሳዊ ተግባር ሲያዘጋጁ በየዘመኑ የነበረውን ሁኔታ ልማድና አስተዳደር የዕቃና የመጣርያ የንዋየ ቅድሳትና የገንዘቡን ዓይነት ሌላውንም ይህንን የመሰለውን ጽፈው ለማቆየት የዘመኑ ሁኔታ ሳያስችላቸው ቀርቷል ወይም ጽፈው ጠፍቶባቸው እንደሆነም እኛ ለማወቅ አልቻልንም ። የደረሰው ምክንያት ሁሉ በዝርዝር ተጽፎ ወደ ዘመናችን ለመድረስ አልቻለም፣ በዚህ ምክንያት የውጭ ሀገር ተወላጆች የሥነ ጽሑፍ ደረጃ ከጐረቤቶቻችን ሀገሮች ከአረቦችና ከግብፃውያን ከግሪክና ከመሳሰሉትም በዝቅተኛነት ደረጃ ለመገመት ገድ ሆኖባቸዋል በማለት በሀገራችን ስለሚገኘው ሥነ ጽሑፍ የራቸውን አስተሳሰብ ገልጸዋል።

እኛም ብንሆን በሀገራችን የተሠራውና የተፈጸመው ሁሉ በሥነ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ እንዳልቀረበ እናውቃለን በሀገራችን የነበሩት የሥነ ጽሑፍ ሰዎች የውጭ ሀገር ባዕዳን በመሆናቸው የቋንቋና የሌላው ችግር ስለሚገጥማቸው ሁሉንም አጣርቶ ለመጻ)ፍ አቅም አይኖራቸውም።

ቄስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ



www.ethiopianorthodox.org

# ማሳሰቢያ

በየአብያተ ክርስቲያናቱ የደረሰውን የልብስ ተክህኖ ችግር ለማቃለልና ለማስወገድ በሥራ ጥናትና ዕቅድ መመሪያ ተጠንቶ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ተፈቀደ፤

1ኛ/ በመናገሻ አውራጃበዓለም ገና ወረዳ አስተዳደር ፣ በሰባታ ቤተ ደናግል ጠበባት ገዳም ።

2ኛ/ በመንበረ ፓትሪያርኩ ጠቅላይ ጽ/ቤት ገቢ የልብሰ ተክህኖ ማደራጃና ማከፋፈያ ከ1970 ዓ.ም ጀምሮ ተቋቁሞ ሥራው በጥሩ ሁኔታ በመካሄድ ላይ ነው ።

የተቋቋመበትም አላማ ለቤተ ክርስቲያን መገልገያ የሚሆኑትን ንዋያተ ቅዱሳት የቤተ ክርስቲያን ማዕከላዊ ጽ/ቤት እያዘጋጀ በልብሰ ተክህኖ በኩል ያለውን ችግር ለማቃለልና ምእመናንንም በከፍተኛ ዋጋ ከነጋዴዎች ከመግዛት ለማዳን ነው።

ስለዚህ የአምስት ልውካን ልብሰ ተክህኖ ዋጋ ብር 200 መሆኑን እየገለጽን ፈላጊዎች በጠቅላይ ቤተ ክህነት እየመጡ መግዛት የሚችሉ መሆኑን እንገልጻለን ።

«ኢትዮጵያ ትቅደም»

ብርሃኑ ገብረ አማኑኤል
የዕቅድና ጥናት ኃላፊ
ስልክ 12-49-09-
ፖ.ሣ. ቁ. 12-83

## ሊቃውንቶቻችን

ከገጽ ፲፰ የዞረ

ንጉሥ ምኒልክ በአንድ በኩል ሶቢ ገደል ከሚባለው ተራራ ላይ ከሠራዊቱ ጋር ሳሉ በ18/76 ዓ.ም. በዘመነ ሉቃስ በመስከረም 10 ቀን ከሌሊቱ 5 ሰዓት ሲሆን በዓፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት ላይ ብርሃን ሰፍሮበት ታየ ።

በዚህም ጊዜ ከላይ እንደተመለከተው በአካባቢው ያሉ ነገሥታትና ከዚያም የነበሩት ሦስት ጳጳሳት እጨጌው ቴዎፍሎስ ቤተ መንግሥቱ የተቃጠለ መስኋቶቸው ከየሠፈራቸው በድንጋጤ ገሥግሠው ከቤተ መንግሥቱ ቢደርሱ እሳት የሌለው ብርሃን ብቻ እንደታላቅ ቤት ቃጠሎ ሆኖ ሲያበራ አይተው ይህ ድንቅ ምሥጢር ምን ይሆን ? እያሉ ተደነቁ ።

በዚህም ሁኔታ ሳሉ ዓፄ ዮሐንስ ከእንግዲህ ወዲህ ይህ ቤት የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት መንገሪያ የመሥዋት መሠዊያ እንጂ የእኔ ሊሆን አይገባውም አሁኑኑ ቡራኬ ይደረግበት ብለው በጳጳሳቱና በእጨጌው ተባረከ ። እንዲህም ሆኖ ሲነጋ በቤተ መንግሥቱ ላይ በሌሊት የታየው ብርሃን ከመዓልቱ የፀሐይ ብርሃን ጋር ተቀላቀለ ።

ከዚህም በኋላ ዓፄ ዮሐንስ ወዲያውኑ ገዥ ድንኳን አስተክለው የሥላሴን ታቦት አስገብተው የቦታውን ስም "አበራ ሥላሴ" ብለውና ደብረው የወሎን ሕዝብ በማስተማር ላይ ለሚገኙት ለሊቁ ለመምህር አካለ ወልድ ከታላቅ አደራ ጋር አስተዳዳሪነቱን ሰጡዋቸው ።

ጉባኤን አስፋፍቶ ለማስተማር ለሊቁ ቦሩ ሜዳ ምቹ ቦታ ሆነላቸው ቀጥሎም ንጉሥ ሚካኤል የአበራ ሥላሴን ቤተ ክርስቲያን እጅግ ደስ በሚያሰኝና በሚያምር ሁኔታ አሠርተው መተዳደሪያውን ሰጥተዋል ።

### የመምህር አካለ ወልድ ደቀ መዛሙርት

የመምህር አካለ ወልድ ደቀ መዛሙርት 500 ያህል ነበሩ ይባላል ። እነዚህንም ሲያስተምሩ ልብስና ቀለብ እየሰጡ ነበር ።

በዚህም አስተያየት በጊዜው በነበረው የትምህርት ፕሮግራም ይዘት የሊቁ ቤት የአዳሪ ትምህርት ቤት" ነበር ሊባል ይቻላል ።

ከአለቃ ዐምደ ጽዮን ተሰማ



# የመጽሐፍ ቅዱስ ዓምድ

፰፡ እግዚአብሔርም፡ የግብፅን፡ ንጉሥ፡
የፈርዖንን፡ ልብ፡ አጸና ፤ እርሱም፡ የእስራኤ
ልን፡ ልጆች፡ አሳደደ፤ የእስራኤልም፡ ልጆች፡
፱፡ ከፍ፡ ባለች፡ እጅ፡ ወጡ ። ግብፆውያንም ፤
የፈርዖን፡ ፈረሶች፡ ሰረገሎቹም፡ ፈረሰኞቹም፡
ሠራዊቱም፡ ሁሉ ፤ አሳደዱአቸው ፤ በባሕሩ፡
ዳር፡ በበኣልዛፎን፡ ፊት፡ ለፊት፡ ባለው፡ በፈ
ሀሒሮት፡ አጠገብ፡ ሰፍረው፡ አገኙአቸው ።
፲፡ ፈርዖንም፡ በቀረበ፡ ጊዜ፡ የእስራኤል፡ ልጆች፡
ዓይናቸውን፡ አነሡ ፤ እነሆም፡ ግብፆውያን፡
በኋላቸው፡ ገሥግሠው፡ ነበር ፤ የእስራኤልም፡
ልጆች፡ እጅግ፡ ፈሩ ፤ ወደ፡ እግዚአብሔርም፡
፲፩፡ ጮኹ ። ሙሴንም፦ በግብፅ፡ መቃብር፡ ስላ
ልነበረ፡ በምድረ፡ በዳ፡ እንሞት፡ ዘንድ፡ አወ
ጣኸንን? ከግብፅ፡ ታወጣን፡ ዘንድ፡ ይህ፡ ያደ
፲፪፡ ረግህብን፡ ምንድር፡ ነው? በምድረ፡ በዳ፡ ከም
ንሞት፡ ብንገዛላቸው፡ ይሻለናል ፤ ተወን ፤
ለግብፆውያን፡ እንገዛ፡ ብለን፡ በግብፅ፡ ሳለን፡
ያልንህ፡ ቃል፡ ይህ፡ አይደለምን? አሉት ።
፲፫፡ ሙሴም፡ ለሕዝቡ፦ አትፍሩ ፤ ዛሬ፡ የምታ
ዩአቸውን፡ ግብፆውያንን፡ ለዘላለም፡ አታዩአ
ቸውምና፡ ቁሙ ፤ ዛሬ፡ ለእናንተ፡ የሚያደርጋ
፲፬፡ ትን፡ የእግዚአብሔርን፡ ማዳን፡ እዩ ። እግዚ
አብሔር፡ ስለ፡ እናንተ፡ ይዋጋል ፤ እናንተም፡
ዝም፡ ትላላችሁ፡ አላቸው ።
፲፭፡ እግዚአብሔርም፡ ሙሴን፡ አለው፦ ለምን፡
ትጮኽብኛለህ? እንዲጓዙ፡ ለእስራኤል፡
፲፮፡ ልጆች፡ ንገር ። አንተም፡ በትርህን፡ አንሣ ፤
እጅህንም፡ በባሕሩ፡ ላይ፡ ዘርጋ ፤ ክፈለውም ፤
የእስራኤልም፡ ልጆች፡ በባሕሩ፡ ውስጥ፡ በየ
፲፯፡ ብስ፡ ያልፋሉ ። እነሆም፡ እኔ፡ የግብፆውያ
ንን፡ ልብ፡ አጸናለሁ፡ በኋላቸውም፡ ይገባሉ ፤
በፈርዖንና፡ በሠራዊቱም፡ ሁሉ፡ በሰረገሎ
ቹም፡ በፈረሰኞቹም፡ ላይ፡ ክብር፡ አገኛለሁ ።
፲፰፡ ግብፆውያንም፡ በፈርዖንና፡ በሰረገሎቹ፡ በፈ
ረሰኞቹም፡ ላይ፡ ክብር፡ ባገኘሁ፡ ጊዜ፡ እኔ፡
እግዚአብሔር፡ እንደ፡ ሆንሁ፡ ያውቃሉ ።
፲፱፡ በእስራኤልም፡ ሠራዊት፡ ፊት፡ ይሄድ፡ የነበ
ረው፡ የእግዚአብሔር፡ መልአክ፡ ፈቀቅ፡ ብሎ፡
በኋላቸው፡ ሄደ ፤ የደመናውም፡ ዓምድ፡ ከፊ
ታቸው፡ ፈቀቅ፡ ብሎ፡ በኋላቸው፡ ቆመ ፤
፳፡ በግብፆውያን፡ ሰፈርና፡ በእስራኤል፡ ሰፈር፡
መካከልም፡ ገባ ፤ በዚያም፡ ደመናና፡ ጨለማ፡
ነበረ ፤ በዚህ፡ በኩል፡ ግን፡ ሌሊቱን፡ አበራ ፤
ሌሊቱንም፡ ሁሉ፡ እርስ፡ በርሳቸው፡ አልተቃ
ረቡም ።
፳፩፡ ሙሴም፡ በባሕሩ፡ ላይ፡ እጁን፡ ዘረጋ ፤ እግ
ዚአብሔርም፡ ሌሊቱን፡ ሁሉ፡ ጽኑ፡ የምሥ
ራቅ፡ ነፋስ፡ አምጥቶ፡ ባሕሩን፡ አስወገደው ፤
ባሕሩንም፡ አደረቀው ፤ ውኃውም፡ ተከፈለ ።
፳፪፡ የእስራኤልም፡ ልጆች፡ በባሕሩ፡ መካከል፡ በየ
ብስ፡ ገቡ ፤ ውኃውም፡ በቀኛቸውና፡ በግራ
ቸው፡ እንደ፡ ግድግዳ፡ ሆነላቸው ። ግብፆው ፳፫፡
ያንም ፤ የፈርዖን፡ ፈረሶችና፡ ሰረገሎች፡ ፈረ
ሰኞቹም፡ ሁሉ ፤ እያሳደዱ፡ በኋላቸው፡ ወደ፡
ባሕር፡ መካከል፡ ገቡ ። ንጋትም፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ ፳፬፡
እግዚአብሔር፡ በእሳትና፡ በደመና፡ ዓምድ፡
ሆኖ፡ የግብፆውያንን፡ ሠራዊት፡ ተመለከተ ፤
የግብፆውያንንም፡ ሠራዊት፡ አወከ ። የሰረገ ፳፭፡
ሎቹንም፡ መንኰራኵር፡ አሰረ ፤ ወደ፡ ጭን
ቅም፡ አገባቸው ፤ ግብፆውያንም፦ እግዚአ
ብሔር፡ በግብፆውያን፡ ላይ፡ ይዋጋላቸዋልና፡
ከእስራኤል፡ ፊት፡ እንሽሽ፡ አሉ ።
እግዚአብሔርም፡ ሙሴን፦ እጅህን፡ በባ ፳፮፡
ሕሩ፡ ላይ፡ ዘርጋ ፤ ውኃውም፡ በግብፆውያን፡
በሰረገሎቻቸውም፡ በፈረሰኞቻቸውም፡ ላይ፡
ይመለስ፡ አለው ። ሙሴም፡ እጁን፡ በባሕሩ፡ ፳፯፡
ላይ፡ ዘረጋ ፤ ባሕሩም፡ ማለዳ፡ ወደ፡ መፍሰሱ፡
ተመለሰ ፤ ግብፆውያንም፡ ከእርሱ፡ ሸሹ ፤ እግ
ዚአብሔርም፡ ግብፆውያንን፡ በባሕሩ፡ መካ
ከል፡ ጣላቸው ። ውኃውም፡ ተመልሶ፡ በኋ ፳፰፡
ላቸው፡ ወደ፡ ባሕር፡ የገቡትን፡ ሰረገሎችን፡
ፈረሰኞችንም፡ የፈርዖንንም፡ ሠራዊት፡ ሁሉ፡
ከደነ ፤ ከእነርሱም፡ አንድ፡ ስንኳ፡ አልቀረም ።
የእስራኤል፡ ልጆች፡ ግን፡ ባባሕሩ፡ ውስጥ፡ ፳፱፡
በየብስ፡ ሄዱ ፤ ውኆችም፡ በቀኛቸውና፡ በግ
ራቸው፡ እንደ፡ ግድግዳ፡ ሆኑላቸው ። እግዚ ፴፡
አብሔር፡ በዚያ፡ ቀን፡ እስራኤልን፡ እንደዚህ፡
ከግብፆውያን፡ እጅ፡ አዳነ ፤ እስራኤልም፡ የግ
ብፆውያንን፡ ሬሳ፡ በባሕር፡ ዳር፡ አዩ ። እስ ፴፩፡
ራኤልም፡ እግዚአብሔር፡ በግብፆውያን፡ ላይ፡
ያደረጋትን፡ ታላቂቱን፡ እጅ፡ አዩ ፤ ሕዝቡም፡
እግዚአብሔርን፡ ፈሩ ፤ በእግዚአብሔርም፡
በባሪያውም፡ በሙሴ፡ አመኑ ።

ምዕራፍ፡ ፲፭ ።

በዚያም፡ ጊዜ፡ ሙሴና፡ የእስራኤል፡ ልጆች፡ ፩፡
ይህን፡ መዝሙር፡ ለእግዚአብሔር፡ ዘመሩ ፤
እንዲህም፡ ብለው፡ ተናገሩ፦
በክብር፡ ከፍ፡ ከፍ፡ ብሎአልና፡ ለእግዚ
አብሔር፡ እዘምራለሁ ፤
ፈረሱንና፡ ፈረሰኛውን፡ በባሕር፡ ጣለ ።
ኃይሌ፡ ዝማሬዬም፡ እግዚአብሔር፡ ፪፡
ነው ፤
መድኃኒቴም፡ ሆነልኝ ፤
ይህ፡ አምላኬ፡ ነው፡ አመሰግነውማለሁ ፤
የአባቴ፡ አምላክ፡ ነው፡ ከፍ፡ ከፍም፡ አደ
ርገዋለሁ ።
እግዚአብሔር፡ ተዋጊ፡ ነው ፤ ስሙ፡ እግ ፫፡
ዚአብሔር፡ ነው ፤
የፈርዖንን፡ ሰረገሎች፡ ሠራዊቱንም፡ በባ ፬፡
ሕር፡ ጣላቸው ፤
የተመረጡት፡ ሦስተኞች፡ በኤርትራ፡
…፡ ባሕር፡ ሰጠሙ ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
ፖስታ ሣጥን ቁጥር 30755
አዲስ አበባ ።



www.ethiopianorthodox.org



እስራኤል ፡ ኤርትራን ፡ ሲሻገሩ ፡ ግብጻውያን ፡ እንደሰጠሙ ፡ ዕብ ፲፩ ፡ ፳፱ ።





# ምእመናን ሆይ !

በክርስቶስ የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን ሀብቶቿ ምእመናን ናቸው የቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን እያፈሰሰ ጉዳት አስከትሏል፤የሥላሴ ፍቅር የጠራችሁ፤ ለቤተ እግዚአብሔር መጠገኛ እጃችሁን እንድትዘረጉ ተጋብዛችኋል ።

የሕትመት ኮሚቴ



www.ethiopianorthodox.org

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ | አ | ዡ | ጊ | ዳ | ኄ | ው | [illegible] |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ | በ | ጉ | ዲ | ሃ | ፄ | [illegible] | [illegible] |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ | ገ | ዱ | ሂ | ዋ | ዜ | ኙ | [illegible] |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ | ደ | ሁ | ዊ | ዘ | ዤ | ሕ | ጦ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ | ሀ | ዉ | ዚ | ዣ | ሔ | ጥ | ጮ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ | ወ | ዞ | ዢ | ሓ | ጤ | ጭ | ዮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ | ዘ | ዦ | ሒ | ጣ | ጬ | ይ | ኮ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ | ዠ | ሑ | ጢ | ጫ | ዩ | ከ | ኾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ | ሐ | ጡ | ጪ | ያ | ኬ | ኽ | ሎ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ | ጠ | ጩ | ዪ | ካ | ኼ | ል | ሞ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ | ጨ | ዩ | ኪ | ኻ | ሌ | ም | ኖ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ | የ | ኩ | ኺ | ላ | ሜ | ን | ኞ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ | ከ | ኹ | ሊ | ማ | ኔ | ኝ | ሶ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ | ኸ | ሉ | ሚ | ና | ኜ | ስ | ሾ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ | ለ | ሙ | ኒ | ኛ | ሴ | ሽ | ዖ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ | መ | ኑ | ኚ | ሳ | ሼ | ዕ | ፎ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ | ነ | ኙ | ሲ | ሻ | ዔ | ፍ | ፡ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ | ኘ | ሱ | ሺ | ዓ | ፌ | ጽ | ቆ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ | ሰ | ሹ | ዒ | ፋ | ጼ | ቅ | ሮ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ | ሸ | ዑ | ፊ | ጻ | ቄ | ር | ፖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ | ዐ | ፉ | ጺ | ቃ | ሬ | ሥ | ቶ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ | ፈ | ጹ | ቂ | ራ | ሤ | ት | ቾ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ | ጸ | ቁ | ሪ | ሣ | ቴ | ች | ኖ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ | ቀ | ሩ | ሢ | ታ | ቼ | ኅ | ጾ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ | ረ | ሡ | ቲ | ቻ | ኄ | ጵ | ፆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ | ሠ | ቱ | ቺ | ኃ | ጴ | ዕ | ፓ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ | ተ | ቹ | ኂ | ጳ | ፄ | ፕ | ጆ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ | ቸ | ኁ | ጺ | ፃ | ፒ | ጅ | ኦ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ | ኀ | ጹ | ፂ | ፓ | ጄ | እ | ቦ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ | ጸ | ፁ | ፒ | ጃ | ኤ | ብ | ጎ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ | ፀ | ፑ | ጂ | አ | ቤ | ግ | ዶ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ | ፐ | ጁ | ኢ | በ | ጌ | ድ | ሆ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ | ጀ | ኡ | ቢ | ጋ | ዴ | ህ | ዎ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ኰ | ኵ | ኲ | ኳ | ኴ |
| ጐ | ጕ | ጒ | ጓ | ጔ |
| ቈ | ቍ | ቊ | ቋ | ቌ |
| ኈ | ኍ | ኊ | ኋ | ኌ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ |
| ቬ | ቭ | ቮ | |

፡ ፤ ፥ ። ? » ! / ) -

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ | ፮ | ፯ | ፰ | ፱ | ፲ | |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | |
| ፳ | ፴ | ፵ | ፶ | ፷ | ፸ | ፹ | ፺ | ፻ | ፲፻ | ፼ |
| 20 | 30 | 40 | 50 | 60 | 70 | 80 | 90 | 100 | 1,000 | 10,000 |

ሏ ሟ ሯ ሷ ሿ ቧ ቷ ቿ ኗ ኟ ዟ ዧ ዷ ጧ ጯ ጿ ፏ ኧ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

## ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ [illegible] [illegible] ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገለግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org